# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

84ኛ ዓመት ቁጥር 015 መስከረም 15 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# “የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አመራሮች የአገልጋይ ሰብዕናን ተላብሰው ሊሠሩ ይገባል”

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አመራሮች ከምንጊዜውም በላይ የአገልጋይ አመራር ሰብዕናን ተላብሰው በውጤታማነት እንዲሠሩ የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንትና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አሳሰቡ።

ብልፅግና ፓርቲ ላለፉት 12 ቀናት በአዳማ ያካሄደው የከፍተኛ አመራሮች የአቅም ግንባታ የሥልጠና መድረክ የፓርቲው ፕሬዚዳንት ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰጡት አቅጣጫ ተጠናቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሥልጠና ማጠቃለያ መርሐግብሩ በሰጡት አቅጣጫ እንደገለጹት፤ ሀገራዊ የመሻገር ትልሞችን በታላቅ ርብርብና ቅንጅት በማሳካት የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር አመራሮች ከምንጊዜውም በላይ የአገልጋይ አመራር ሰብዕናን ተላብሰው በውጤታማነት ሊሠሩ ይገባል፡፡

ፓርቲው “የሕልም ጉልበት ለእመርታዊ እድገት” በሚል መሪ ሀሳብ ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ከፌዴራል ተቋማት ለተውጣጡ ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ከፍተኛ የአመራር አባላቱ፣ የነገዋን ኢትዮጵያ ብልፅግና በማረጋገጥ የትውልዱን መፃኢ ዕድል ምቹና ስኬታማ ማድረግ በሚያስችሉ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ባላቸው ሀሳቦች ዙሪያ ሥልጠና ሰጥቷል ብለዋል።

ሥልጠናው የአመራር አባላቱ ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም የሕዝብ ችግሮችን በየደረጃው በመፍታት በተግባር አንድነት የኢትዮጵያን ከፍታ ለማረጋገጥ በሥልጠናው በቂ አቅም ያገኙበትና የነገዋን ኢትዮጵያ መሥራት የሚያስችል ግንዛቤ የጨበጡበት እንደነበረ ገልፀዋል።

ሥልጠናው ሀገር ቀያሪም፣ ሀብት ፈጣሪም ሰው

"የበለፀገች ኢትዮጵያን... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



አቶ ጌታቸው ቢያዝን

# በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች የመማር ማስተማር ሥራውን ከማደናቀፍ እንዲታቀቡ ቢሮው አሳሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ትምህርት ከየትኛውም ፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች የመማር ማስተማር ሥራውን ከማስተጓጎል እንዲቆጠቡ

በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ኢሬቻ - የኅብር ትዕምርት

**ማርቆስ በላይ**

የኢሬቻ በዓል በየዓመቱ በመስከረም ወር በድምቀት እንደሚከበር ይታወቃል፡፡ በተለይም በሆረ ፊንፊኔና በቢሾፍቱ ሆረ አርሰዲ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ በተሰበሰበበት በድምቀት ይከበራል፡፡ ለመሆኑ የኢሬቻ በዓል ታሪካዊ መሠረትና አከባበር፤ በዓሉ ለኦሮሞ ሕዝብ ያለው ጠቀሜታ ምንድነው? ስንል የዘርፉን ምሑራን አነጋግረናል፡፡

በኦሮሞ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የኦሮሞ ሥነ ጽሑፍ ፎክሎር ተመራማሪ ጌታቸው አበራ ለኢትዮጵያ

ኢሬቻ- የኅብር... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ምርታማነት ላይ የተደቀነው የአፈር አሲዳማነት ፈተና

**ታደሠ ብናልፈው**



ሰብሎች ለማደግና ፍሬ ለመስጠት በአፈር ውስጥ የሚገኘውን ንጥረ ነገር ሁሉ ይመገባሉ፡፡ በሥራቸው አማካኝነት ያገኙትን ንጥረ ነገር ሁሉ ይመገባሉ። በዚህ ሂደት አላስፈላጊ ንጥረ ነገሮችንም ጭምር ወደ ውስጣቸው በማስገባት ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ በሀገራችንም አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በእድገታቸውና በፍሬማነታቸው ላይ ስጋት የደቀነ ክስተት እየተፈጠረ ነው፡፡ ለዚህ መነሻው ደግሞ የአፈር አሲዳማነት ነው፡፡

በኢትዮጵያ እየተባባሰ የመጣው የአፈር አሲዳማነት

ምርታማነት ላይ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል




# የሠላም አምባሳደሮች

ልጅዓለም ፍቅሬ



ወይዘሮ ሲዲያ ግርማ



ወይዘሮ እህታለም ዓለሙ



ወይዘሮ የውብዳር ከተማ



ወይዘሮ ወይንሸት ኬሜ

ፎቶ - ሃዲሽ አብርሃ

ዜና ሐተታ

ሃይማኖታዊም ሆኑ ባሕላዊ በዓላት የጋራ ዕሴት የሚያዳብሩና ለማኅበራዊ መስተጋብር የቀኝ እጅ በመሆን ስለሠላም የሚሰብኩ ናቸው። ኢትዮጵያውያን ደግሞ በዚህ ብዙ ልምድ አላቸው፡፡ የተለያዩ ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊ ዕሴቶች፣ ወግና ልማዶች ለዚህ ማሳያዎች ይሆናሉ፡፡

ወርሐ መስከረም ኢትዮጵያውያንን በገመደው ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴቱ በኩረ ወራት የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ከእነዚህም ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት መካከል የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የዘመን መለወጫ በዓላት፣ መስቀልና ኢሬቻ በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው።

በመስከረም ተስፋ፣ ልምላሜ፣ ቸርነት፣ ምሕረት፣ ይቅርታ፣ ቃልኪዳንና እምነት በሰው ልጆች ልቦና ሰፊ ቦታ አላቸው፡፡ ማኅበራዊ እሴቶች ለሰው ልጆች ጠንካራ ሥነልቦናዊ ውቅር ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ከበዓላቱ ትሩፋት ለመቋደስና እኩይ ዓላማ ያነገቡ የሴረኞችን ሃሳብ ማምከን የሁሉም ኃላፊነት ቢሆንም ሴቶች በዚህ ጉዳይ ባለጥምር ድል ተጋሪዎች ናቸው፡፡

ሴቶች የማኅበረሰቡ ግማሽ አካል መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ባላቸው ተፈጥሯዊ ብልሃት የማኅበረሰቡን ሠላም ለማጽናት ልዩ ተሰጥዖ ተችሯቸዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮም ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሁሉም ክፍለ ከተሞች ከተውጣጡ የመዲናዋ ሴቶች ጋር "ሴቶች ለሠላም፣ ሠላም ለሴቶች" በሚል መሪ ሃሳብ በመስቀል፣ በዳመራና በኢሬቻ በዓላት አከባበር ዙሪያ የውይይት መድረክ አካሂዷል፡፡

በዓላቱ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ይዘታቸው ጠብቀው እንዲከበሩ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የበኩላቸውን ለመወጣት ቁርጠኛ መሆናቸውን ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡ የመዲናዋ ሴቶች ይናገራሉ፡፡

ወይዘሮ እህታለም ዓለሙ በቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ስድስት ነዋሪ ናቸው፡፡ የሴትነት ብልሃትን በመጠቀም ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ መስጠት በአደባባይ በዓላቱ ከሴቶች የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው ይላሉ፡፡ በበዓላቱ ፀረ-ሠላም ኃይሎችን እንዴት መግታት ይቻላል የሚለው ከታችኛው የሴቶች መዋቅር ጀምሮ ሲሠራ መቆየቱን ያብራራሉ፡፡

ሠላም ለሰው ልጅ የመኖር ዋስትና ነው የሚሉት ወይዘሮ እህታለም፤ የመዲናዋ ሴቶችም ይህንን በመገንዘብ በነቂስ ወጥተው እየተሳተፉ እንደሚገኙ ይጠቁማሉ። ለሠላም ዘብ መሆን እና የሠላም ኃይላትም እጅ በእጅ በመያያዝ በአብሮነት መቆም እንደሚያስፈልግ መክረዋል፡፡

ለበዓሉ የሚመጡ እንግዶች ሠላም ከማስጠበቅ በተጨማሪ መንገድ የጠፋቸው እንግዶች መንገድ የመጠቆም እንዲሁም ሆቴሎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምንም አይነት የዋጋ ጭማሪ እንዳያደርጉ በየአካባቢው ክትትል እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ አንድ ነዋሪ ወይዘሮ የውብዳር ከተማ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው በተለይ ወንጀልን ከመከላከል አንጻር በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉ ሲሆን በመጪው በዓላትም ሠላም ለማስፈን ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ይናገራሉ፡፡

እንደ ወይዘሮ የውብዳር ገለጻ፣ በክፍለ ከተማው ለስጋት ተጋላጭ የሆኑና ዳመራ የሚደመርባቸው ቦታዎች ተለይተዋል፡፡ ለበዓላቱ የሚመጡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ያለምንም እንግልት በሠላም እንዲያከብሩ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠው እየተሠራ ነውም ይላሉ፡፡

ሴት ልጅ በማኅበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ የመፍጠር ችሎታ አላት የሚሉት ወይዘሮ የውብዳር፣ ይህንንም ዕድል ወደ ውጤት በመቀየር ለበጎ ዓላማ ማዋል ይገባልም ባይ ናቸው፡፡

የአደባባይ በዓላቱ በሠላም ተከብረው የሚፈለገውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሴቶች ለሠላም ቅድሚያ ሰጥተው የነቃ ተሳትፎ ሲያደርጉ ነው ያሉት ደግሞ የሠላም ሠራዊት አባል ወይዘሮ ወይንሸት ኬሜ ናቸው፡፡

በዓላቱ በተገቢው መልኩ ተከብረው እንዲጠናቀቁ ለፀጥታ አካላት የተደራጀ መረጃ መስጠትና ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ ከመፍጠር ረገድ ከወዲሁ ወደ ሥራ መገባቱን ያስረዳሉ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ በበኩላቸው ከዚህ በፊትም በመዲናዋ ሴቶች ከፀጥታ አካላት ጋር ተቀናጅተው በመሥራታቸው ውጤታማ መሆን እንደተቻለም ይናገራሉ።

የከተማዋ የሠላምና ፀጥታ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል የሚሉት ወይዘሮ ሊዲያ፤ በተለይ በከተማው የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ አስተዋፅዖ ማበርከቱን ያክላሉ፡፡

ሴት ልጅ በተሰማራችበት መስክ ሁሉ የፈጻሚነት አቅም፣ የማስተባበር ችሎታ እንዲሁም ማኅበረሰብ አቀፍ ውይይቶች በበላይነት የመምራት አቅም ያላት መሆኗ በሠላም ዙሪያ ያላት ሚና የላቀ እንደሚያደርገው ይጠቁማሉ፡፡

የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት በቱሪዝሙ ዘርፍ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ እምርታ የሚያመጡና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ፍሰት የሚጨምሩ በመሆናቸው በዓላቱ በሠላም እንዲጠናቀቁ ሴቶች በንቃት መሳተፍ እንደሚጠበቅባቸው ያስገነዝባሉ፡፡



ኒጎር ጆሴፍ አኮክ



መሐመድ ጋሳብ

## በቱሪዝም ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር ለጋራ ተጠቃሚነት በትብብር እንደሚሠሩ የደቡብ ሱዳን እና የጅቡቲ ልዑካን ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በቱሪዝም ዘርፍ በስፋት እየሠራች ካለችው ኢትዮጵያ ጋር ሁለንተናዊ ትብብር በማድረግ ለጋራ ተጠቃሚነት እንሠራለን ሲሉ በኢጋድ አባል ሀገራት የቱሪዝም ጉባኤ ላይ የተሳተፉት የደቡብ ሱዳን እና የጅቡቲ ልዑካን አባላት ተናገሩ።

በአዲስ አበባ በተካሄደው በዚሁ ጉባኤ ላይ ከተገኙት የአባል ሀገራቱ ተወካዮች መካከል የደቡብ ሱዳንና የጅቡቲ ልዑክ አባላት ዘላቂ የቱሪዝም ፍኖተ ካርታው ለቀጣናው ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት መልካም ዕድል ይዞ የሚመጣ መሆኑን ተናግረዋል።

በቱሪዝም ዘርፍ በስፋት እየሠራች ካለችው ኢትዮጵያ ጋር ሁለንተናዊ ትብብር በማድረግ ለጋራ ተጠቃሚነት በቁርጠኝነት የሚሠሩ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

በደቡብ ሱዳን የምሥራቅ አፍሪካ ማኅበረሰብ ጉዳዮች ሚኒስቴር የንግድና ኢንቨስትመንት ተቆጣጣሪ ኒጎር ጆሴፍ አኮክ፤ የቱሪዝም ፍኖተ ካርታው ለቀጣናው ሀገራት የቱሪዝም እምርታ መልካም አጋጣሚ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

ደቡብ ሱዳን በዘርፉ ልማትና ተጠቃሚነት ዙሪያ ከኢትዮጵያ ጋር ይበልጥ ተቀራርባና ተባብራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኗንም ገልጸዋል።

በጅቡቲ የአስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት መሐመድ ጋሳብ፤ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ተመጋጋቢ የቱሪዝም ሀብቶችን በማልማት ለጋራ ተጠቃሚነት የጀመረው ጥረት ጥሩ ጅምር መሆኑን ገልጸዋል።

በዘርፉ ልማትና የጋራ ተጠቃሚነት የኢትዮጵያን የልማት ጥረቶች አድንቀው በዚህ ረገድ አብሮነትና ትብብራችን ይቀጥላል ብለዋል።

የቀጣናው ሀገራት እምቅ የቱሪዝም ሃብታቸውን በጋራ አልምቶ ለመጠቀም የጀመሩት ጥረትም ትልቅ ተስፋ የሰነቀ መሆኑን ተናግረዋል።

የሁለቱም ሀገራት ተወካዮች የኢትዮጵያን የቱሪዝም ልማት ጥረት በማድነቅ በትብብር ለመሥራት ዝግጁ ነን ሲሉ አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን በቱሪዝም ዘርፍ በተለይም በፓርኮች ልማት በትብብር መሥራት የሚችሉባቸው ዕምቅ አቅም እንዳላቸው ኒጎር ጆሴፍ ገልጸዋል።

በጅቡቲ የአስጎብኚ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት መሃመድ ጋሳብ በየብስ፣ በባቡር እና በአየር ትራንስፖርትና በቱሪዝም ልማት ኢትዮጵያና ጅቡቲ በጋራ ቢሠሩ ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል። ይህም ጎብኚዎች ሁለቱንም ሀገራት ለመጎብኘት ምቹ እንደሚያደርገው ተናግረዋል።

የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና በተለያዩ ችግሮች እየተፈተነ ቢሆንም በእምቅ የተፈጥሮ ሃብት፣ ባሕላዊና ታሪካዊ ፀጋዎች የታደለ መሆኑ ይታወቃል።

በመሆኑም በቀጣናው ያለውን እምቅ ሃብት በጋራ አልምቶ ለመጠቀም የምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት ባለሥልጣን /ኢጋድ/ አባል ሀገራትን ማዕከል ያደረገ የ10 ዓመታት የዘላቂ ቱሪዝም ፍኖተ ካርታ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል።

## ከ16 ሺህ በላይ ወጣቶች የመስቀልንና የኢሬቻን በዓል በማስተባበር ይሳተፋሉ

ሠላማዊት ውቤ



ወጣት ፎሊ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- የፊታችን ሐሙስ መስከረም 16 በሚከበረው የደመራ በዓል እንዲሁም መስከረም 25 ቀን 2017 በመዲናችን አዲስ አበባ በሚከበረው የኢሬቻ በዓል በማስተባበር ከ16 ሺ በላይ የማኅበሩ አባላት ከዝግጅቱ ጀምሮ በሂደቱ እየተሳተፉ እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር ገለጸ፡፡

የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት ወጣት ፎሊ ንጉሤ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለፀችው፤ ማኅበሩ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የማኅበሩ አባላትና የከተማው ወጣት በነቂስ ወጥቶ ሀገር አቀፍ በዓላትን በበጎ ፈቃድ እንዲያስተባብርና ለሠላም ዘብ እንዲቆም ማድረግ ነው፡፡

በያዝነው የበጋ ወራት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትም ከራሱ ጀምሮ በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የሠላም ማስከበር ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝበት ሁኔታ መኖሩን አመልክታለች፡፡

የፊታችን ሐሙስ የሚከበረው የደመራ በዓል እና በዚሁ ወር የሚከበረው የኢሬቻ በዓል የአደባባይ በዓል እንደመሆናቸው ለብዙ ነገር ተጋላጭ መሆናቸውን ጠቁማ በሠላም ተጀምረው በሠላም እንዲጠናቀቁ ማኅበሩ፤ ከዝግጅቱ ጀምሮ እያስተባበረ እንደሚገኝ አስታውቃለች፡፡

ማኅበሩ በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የራሱ አደረጃጀት ያለው መሆኑን ጠቁማ፤ ከሚመለከታቸው የሠላምና ፀጥታ አካላት፤ ከቢሮና ከማኅበረሰቡ ጋር በመቀናጀት የአካባቢውን ሠላም የሚያስጠብቅበት ሁኔታ እንዳለም ገልጻለች፡፡ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ በበዓላቱ ላይ እንዲሳተፍ፤ ግንዛቤዎችን የመፍጠር፤ የማነቃቃት ሥራዎችን እየሠራ መገኘቱንም አስረድታለች፡፡

“ማኅበራችን የብዙኃን ወጣቶች ማኅበር ነው” ያለችው ምክትል ፕሬዚዳንቷ ወጣት ፎሊ፤ በተለይም ደግሞ በበጎ ፈቃድ በስፋት የሚሠራባቸው ሂደቶች ስላሉ በወጣቱ ከዚህ በፊት ሲፈጠር የነበረው ግንዛቤ ሄዶ አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል ጋር የደረሰበት ሂደት መኖሩንም አብራርታለች። ይሄን የበጎ ፈቃድ ፅንሰ ሀሳብም ሁሉም ወጣት ወስዶና በነቂስ ወጥቶ የበጎ ፈቃድ ተግባር እንዲያከናውንም ጥሪዋን አስተላልፋለች፡፡


የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ ከተማ አስተዳደር ለረጅም ዓመታት በዕቅድ ተይዞ እየተሠራበት መሆኑን የጠቆመችው ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ ባለፈው 2016 ዓ.ም የተለያዩ በጎ ፈቃድ ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ ደረጃ ተይዞ የተገባበት ሁኔታ የነበረ መሆኑንም አስታውሳለች፡፡

ወጣት ፎሊ ንጉሤ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ ከተማ አስተዳደር ለረጅም ዓመታት በዕቅድ ተይዞ እየተሠራበት መሆኑን ጠቁማ፤ ባለፈው 2016 ዓ.ም የተለያዩ በጎ ፈቃድ ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ ደረጃ ተይዞ የተገባበት ሁኔታ የነበረ መሆኑንም ተናግራለች፡፡

የማጠናከሪያ ትምህርት፤ የተለያዩ የአይሲቲና አጫጭር ኮርስ ሥልጠናዎችን፤ ደም ልገሳ፤ ቤት እደሳ፤ ማዕድ ማጋራት፤ ኮሪደር ልማት ያሉ ሰብዓዊ አገልግሎቶች በበጎ ፈቃደኛ ወጣቱ በነፃ ሲከናወኑ መቆየታቸውን አብራርታለች። በዚህም ማኅበሩ ለማከናወን ካቀደው ከ75 በመቶ በላይ ለማሳካት ስለመቻሉም ጠቅሳለች ፡፡

የክረምት በጎ ፈቃድ ሥራው በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው ያልተዘጋና እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑን ጠቁማም የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት ትምህርት ቤት በመከፈቱና አንዳንድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች በመጠናቀቃቸው የተዘጉ መሆናቸውንም ተናግራለች፡፡

“ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያይዞ ከተማችን የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ የተለያዩ የልማት ሥራዎች በተለያዩ ወቅቶች ይሠራሉ” ያለችው ምክትል ፕሬዚዳንት ፎሊ፤ ከክረምቱ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሳይዘጋ በበጋውም የቀጠለው ይሄው የኮሪደር ልማት ስለመሆኑ አስታውቃለች፡፡



አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)

## በመስከረም ወር የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት የኢትዮጵያን የተሟላ ገጽታ ለዓለም የሚገልጡ ናቸው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በመስከረም ወር የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት የኢትዮጵያ የተሟላ ውበት ለዓለም የሚገልጡ መሆናቸውን የቱሪዝም ከፍተኛ ባለሙያው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ገለጹ።

የቱሪዝም ከፍተኛ ባለሙያው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በመስከረም ወር የሚከበሩ እንደመስቀል፣ የኦሮሞ ሕዝብ ትውፊታዊ መገለጫ እሬቻ፣ የወላይታ የዘመን መለወጫ ዮዮ ጊፋታ፣ የሀዲያ የዘመን መለወጫ ያ ሆዴ እና ሌሎችም የአደባባይ በዓላት የኢትዮጵያን የተሟላ ገጽታና ውበት ለዓለም የሚገልጡ ናቸው።

የአደባባይ በዓላት ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነው የሚያከብሯቸው በመሆኑ እርስበርስ ለመተሳሰር እና የየራሳቸውን ባሕልና ትውፊት ለሌሎች ለማስተዋወቅ ያገለግላሉ ያሉት አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)፤ ለአብነት የመስቀል ደመራ በዓል በዩኔስኮ በማይዳሰስ ቅርስ ተመዝግቦ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘ በመሆኑ በርካታ ቱሪስቶች እንደሚታደሙበት ገልጸዋል።

ሌሎቹንም የአደባባይ በዓላት ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ በማድረግ የቱሪስት ቁጥርን ማሳደግ ይገባል ያሉት አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)፤ ይህም ለሥራ ዕድል፣ ለውጭ ምንዛሪ ግኝት እና ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ የቱሪስት መስሕብ ሥፍራዎችን ለማስተዋወቅ እገዛ ያደርጋል ነው ያሉት።

የአደባባይ በዓላቱን ለመታደም የሚመጡ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኝዎችን ለማስተናገድ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ አለባቸው ያሉት አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)፤ በዓላቱ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴታቸውን በሚያጎላ መልኩ እንዲከበሩ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

በተለይ የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ እና ባለድርሻ አካላት በዓላቱን ለዓለም ይበልጥ ማስተዋወቅ እንደሚኖርባቸው ገልጸው፤ የቱሪዝም ዘርፉ ይበልጥ ተጠናክሮ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው እያደገ እንዲመጣ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በዓላቱ ቱሪስቶችን ከመሳባቸውም በላይ በኢትዮጵያ ያለውን የቱሪዝም ዕምቅ አቅም ለማሳወቅና ሀገርን ለዓለም ለማስተዋወቅ ይረዳል። ሀገሪቱን በልማት ወደፊት ለማምጣት ቱሪዝም አንዱ መንገድ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህ ደግሞ ከመንግሥት በተጨማሪ ባለሃብቶችና ኅብረተሰቡ የጀመሩትን ጥረት ሊያጠናክሩ እንደሚገባ አመልክተዋል።

## የአካል ጉዳተኞች አካታችነት እስከምን?

ነፃነት ዓለሙ




ከኮሪደር ልማቱ ጋር በተያያዘ አዳዲስ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እየተስፋፉ መምጣታቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እነዚህ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከተማውን ከማስዋብና ከማዘመናቸውም ባለፈ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረጉ ረገድ አንዳንድ ለውጦች እንዳሉ የሚያሳዩ የመንገድ ዲዛይኖችና አንዳንድ ግንባታዎች እየታዩ ነው፡፡

ለመሆኑ እነዚህ ዲዛይኖች፣ የመንገድ ሥራዎች እና ሌሎች የሕንፃና የመሳሰሉት ግንባታዎች በታሰበላቸው ዓላማ ልክ ለአካል ጉዳተኞች ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ ነው?

የአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ገለታው ሙሉ፤ አካል ጉዳተኞችም በኮሪደር ልማቱ እንደ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልፀው ትልቁ ጥያቄያቸው ተደራሽነት ከመሆኑ አኳያ በተለይ የመንገድ ልማቱ መልካም አጋጣሚ በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው ብለዋል።

ይህ ማለት ግን ፍፁም ችግር የለበትም ማለት አይደለም የሚሉት ፕሬዚዳንቱ እስካሁን ከተማችን ላይ ከነበሩት ከፍተኛ የመሠረተ ልማትና የመረጃ አውታሮች ችግር አንፃር ኮሪደር ልማቱ ላይ እየታዩ ያሉ በጎ ነገሮች አሉ፤ ነገር ግን ደረጃውን ጠብቆ ከመሥራት አንፃር ችግር አለ ይላሉ፡፡

ለምሳሌ በእግረኛ መንገድ ላይ ለዓይነ ስውራን መንገድ መምሪያ ተብለው የተሠሩትን ቢጫ መስመሮች ስናይ አልፎ አልፎ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ደረጃቸውን ጠብቀው የተሠሩ እንዳሉ ብዙ ቦታዎች ላይ ደግሞ ደረጃቸውን ጠብቀው ባለመገንባታቸው ምክንያት ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ ያብራራሉ። አንዳንዴም መስመሩ ላይ ሌላ ነገር የማስቀመጥ ሁኔታዎች እንዳሉ መታዘባቸውንም ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም የእግረኛ ማቋረጫ ዜብራዎች ዳርና ዳር ባሉ የእግረኛ መንገዶች መሐል አንድ የዊልቸር ተጠቃሚ በቀጥታ ተሻግሮ ወደ እግረኛ መንገዱ ለመውጣት የሚያስችል ተደርጎ ከመሥራት አንፃርም አብዛኛው ቦታ ችግር መኖሩን የሚገልፁት ፕሬዚዳንቱ አንዳንድ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ሄዶ አገልግሎት ለማግኘትም ለአካል ጉዳተኞች አስቸጋሪ መሆኑን ያነሳሉ።

በተለይ ደረጃውን የጠበቀና አካል ጉዳተኞችን የሚያካትት ከመሆን አኳያ የሚቀር ነገር እንዳለ ጠቅሰው የተጀመሩ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በቀጣይ ሥራዎችም በተቻለ መጠን ሁሉን አቀፍ የሆነ እና አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረገ ሥራ እንዲከናወን ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት ኢንጅነር እያሱ ሰለሞን በበኩላቸው ከተማችን ገና እየለማች ከመሆኑ አንፃር ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ ጠቅሰው በሂደት እየተስተካከሉ እንደሚሄዱ ይገልፃሉ፡፡ ባለሥልጣኑ አዳዲስ መንገዶችን በሚሠራበትና ነባር መንገዶች ላይ ማሻሻያ በሚያደርግበት ጊዜ አካልጉዳተኞችን ታሳቢ እንደሚያደርግም ይገልፃሉ።

በፊት ከነበረው አኳያ ለውጦች እንዳሉም አይካድም ይላሉ፡፡ ከዚህ ባሻገርም ለእነሱ በተሠሩ መንገዶች ላይ የቆሻሻ መጣያ በማስቀመጥ፣ ችግኝንና ሌሎችም ነገሮችን በመትከል ለታሰበለት ዓላማ እንዳይውል መደረጉን ከመከላከል አንፃር ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠሩ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

በ2016 ዓ.ም ኮሪደር ልማቱን ሳይጨምር ከ40 ኪሎሜትር በላይ የእግረኛ መንገድ ግንባታ ተከናውኗል። አሁን ላይ እንደበፊቱ ተሽከርካሪ ብቻ የሚተላለፍባቸው መንገዶች ላይ ትኩረት መስጠት ሳይሆን መንገድ ለሁሉም የሚል እሳቤ ተይዞ የከተማዋን መንገዶች በዛ ደረጃ መሥራት ከጀመርን ዓመታት አልፈዋልም የሚሉት ኃላፊው የኮሪደር ልማቱ ደግሞ የበለጠ ይህንን አጠናክሮ የሚሄድ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ለዓይነስውራን መተላለፊያ የሚሆኑት መንገዶችም ለዚህ ማሳያ መሆናቸውን ጠቅሰው ባለሥልጣኑ ከዚህ በመነሳት ወደፊት የተሻሉ ሥራዎችን እንደሚሠራም ይገልፃሉ፡፡ ለ2017 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ አዳዲስ በሚገነቡ እንዲሁም በነባር መንገዶች ማሻሻያ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ላይ ባለሥልጣኑ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራም ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኢንጅነር መቆያ ዓለማየሁ ከኮሪደር ልማቱ ጋር በተያያዘ አዳዲስ ሕንፃዎች ሲገነቡ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆኑ እየሠሩ እንዳለ ይገልፃሉ፡፡

የድሮ ሕንፃዎችን በማደሱ ረገድም ቢሮው አንዳንድ ለይስሙላ የተቀመጡ የአካል ጉዳተኛ መገልገያዎችን የማስተካከል ሥራዎችን እየሠራ እንዳለ ጠቅሰው የኮሪደር ልማቱ አንዱ ዓላማ ከተማውን ማዘመን ስለሆነ ሕንፃዎች የሚገነቡት ወይንም የሚታደሱት አካል ጉዳተኞችን ከግንዛቤ በማስገባት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡



## ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓቱ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን እያዳከመው ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት ተግባራዊ በመደረጉ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ እየተዳከመ መምጣቱን የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ላኪዎች ማኅበር አስታወቀ።

የማኅበሩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ዲና ገዛኸኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ባለፉት ዓመታት በርካታ የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት በኮንትሮባንድ መንገድ ከሀገር ውጭ እንዲወጡ ይደረጋል። ይህም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባት ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል።

በተቃራኒው ደግሞ በኮንትሮባድ ሥራ ላይ ወይም ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ላይ የሚሳተፉ አካላት ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኙ አድርጓል ያሉት አቶ ዲና፤ በአሁኑ ጊዜ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ጋር ተያይዞ ተግባራዊ የተደረገ ያለው ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት ኢትዮጵያ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ያደርጋታል ብለዋል።

ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት ተግባራዊ በመደረጉ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ እየተዳከመ መጥቷል ያሉት አቶ ዲና፤ ይህም ሕጋዊ የቁም እንስሳት ንግድ እንዲነቃቃ አድርጓል። ከዚህም ባለፈ በሕጋዊ መንገድ የሚሳተፉ ላኪዎችን አቅምና የሥራ ተነሳሽነት እያሳደገ መምጣቱን ገልጸዋል።

የቁም እንስሳት ንግድ በኮንትሮባንድ ተውጦ የቆየ በመሆኑ መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት መስጠት አለበት ያሉት አቶ ዲና፤ ሕገወጥ የኮንትሮባንድ ንግዱ ከማኅበሩ አቅም በላይ በመሆኑ ማኅበሩ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎት ቆይቷል። ይህም የማኅበሩ አባላት በዘርፉ ተስፋ እንዲቆርጡ አድርጎት ነበር ነው ያሉት።

አሁን ላይ ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሥርዓት ተግባራዊ በመደረጉ በጥቁር ገበያው እና በባንኮች መካከል ያለውን የውጭ ምንዛሪ ልዩነት አጥብቦታል ያሉት አቶ ዲና፤ ይህም የቁም እንስሳት በአነስተኛ የውጭ ምንዛሪ በኮንትሮባንድ መንገድ እንዳይሸጡ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

ሌላው በሕገወጥ መንገድ የቁም እንስሳትን በመሸጥ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ በጥቁር ገበያ ይመነዘር እንደነበር ያነሱት አቶ ዲና፤ ይህም በሀገር ውስጥ ገበያው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድር መቆየቱን ገልጸዋል። አሁን ግን መንግሥት ባደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ችግሩ እየቀነሰ መምጣቱን አስረድተዋል።

በአጠቃላይ አሁን ላይ የቁም እንስሳትን በጫካ ወስዶ ከመሸጥ ይልቅ በሕጋዊ መንገድ መሸጥ ተመራጩ መንገድ እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል።

## ተጠየቅ

# “የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከ300 ቢሊዮን ብር በላይ ያልተከፈለ ዕዳ አለበት”

- አቶ ሽፈራው ተሊላ ፣
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር



**የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን**

**ክፍል ሁለት**

**የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዘመናዊ የመሠረተ ልማት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በመኖሪያ እና በንግድ ቤታችን ውስጥ ለተለያዩ ተግባራት ጥቅም ላይ ይውላል። የኃይል ፍላጎት በየጊዜው እየጨመረ ባለበት በዚህ ጊዜም፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት አገልግሎቱን አስተማማኝ እና ዘላቂ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋማት የኤሌክትሪክ ኃይልን የማመንጨት፣ የማስተላለፊያ እና የማሰራጨት ኃላፊነት አለባቸው፣ ይህም ተቋማቱን በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ የተቆራኙ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።**

**በዓለም አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት አስፈላጊ ኃይልን ከመስጠት በተጨማሪ ዘላቂነት እና ፈጠራ ላይ ያተኩራሉ። እንደ ፀሐይ እና ንፋስ ያሉ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ በማዘመን የአካባቢን ተፅእኖ የሚቀንሱ ንፁህ ቴክኖሎጂዎችን ለማካተት ስልቶችን ይቀይሳሉ። የዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴያቸው የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን፤ በታዳሽ ኃይል ዘርፍ የሥራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ እድገትን ይደግፉበታል።**

**በዚህ ተለዋዋጭ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት የቁጥጥር ሥርዓት ለውጦች በማድረግ እና መሠረተ ልማት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን መቅረፍ ከቻሉ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ ይችላሉ። እኛም ይህንኑ ሃሳብ ይዘን ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመሄድ ስለ ተቋሙ የአስተዳደር ሥርዓቶች፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት፤ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች እና የኦዲት ሪፖርቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽፈራው ተሊላ አቅርበን፤ ባለፈው ሳምንት የክፍል አንድ ዝግጅታችንን ለንባብ ማብቃታችን የሚታወስ ነው። ዛሬ ደግሞ የመጨረሻውን ክፍል (ክፍል ሁለት) እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ!**

**አዲስ ዘመን፡- “ስማርት” ቆጣሪዎችን ከማሰራጨት አንጻር እንዴት እየተሰራ ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** የደንበኞችን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን ተቋማችን በስፋት እየሰራባቸው ከሚገኙት ጉዳዮች መካከል በቴክኖሎጂ የበለጸጉ “ስማርት” ቆጣሪዎችን ለማኅበረሰቡ ማሰራጨት አንደኛው ነው። ቴክኖሎጂው የደንበኛውንም ሆነ የተቋሙንም ስራ የሚያቃልል ሲሆን፤ ደንበኛውና ተቋሙ አስተማማኝ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያግዛል። ቀደም ብሎ የነበሩት ቆጣሪዎች የተቋማችን ሰራተኞች ሄደው ካነበቧቸው በኋላ ነው ወደ ሲስተም የሚገቡት።

በንባብ ላይ ደግሞ ስህተት ሊከሰት ይችላል። ይህም ያልተገባ ዋጋ ሊፈጠር ስለሚችል በደንበኛውና በተቋሙ ግኝኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህን ለማስተካከል ነበር ቆጣሪዎቻችንን ወደ ስማርት ቆጣሪዎች ለመቀየር የሰራነው። አሁን ላይ ስማርት ቆጣሪዎችን የሚፈልጉ በርካታ ደንበኞች ስላሉ የበፊቶችን ቆጣሪዎች በአንድ ጊዜ መቀየር አይቻልም። ነገር ግን ሂደት የሚተገበር ይሆናል። ምክንያቱም ትልቅ ኢንቨስመንት የሚጠይቅ በመሆኑ።

ስማርት ቆጣሪዎችን ከመተካት አንጻር በመጀመሪያ ላይ ቁልፍ ደንበኞች ለሚባሉት እና ለሀገሪቷ የኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ በሚያበረክቱ ደንበኞችን ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን ነው። ወደ 40 ሺህ ለሚጠጉ የኢንዱስትሪ ደንበኞች እና ትልልቅ ተቋማት በስማርት ቆጣሪ እየተቀየርን ነው።

የኢንዱስትሪ ደንበኞች በቁጥር ትንሽ ቢሆኑም የፍጆታ መጠናቸው ግን ከፍተኛ ነው። ቀጥሎም ሶስተኛ ደረጃ (three phase) ደንበኞች የሚባሉ አሉ። የንግድ ተቋማትን ወደዚህ ይቀየራሉ። በ2017 ወደ 125 ሺህ ደንበኞች የስማርት ቆጣሪዎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል። የቆጣሪዎች ግዥ ተከናውኖ ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ ነው፤ ገብቶ እንዳለቀ ስማርት ቆጣሪውን የመትከል ስራ ይከናወናል። በቀጣይም በሂደት ትንንሽ ደበንበኞችን የመቀየር ስራ እንሰራለን።

ስማርት ቆጣሪዎች በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን፤ ከእነዚህ ጥቆሞች መካከልም በሁለቱ ወገኖች (በአገልግሎት ሰጭው እና በደንበኛው) መካከል የሚኖረውን ግኑነት ያሳልጣል። ይህ ማለት የደንበኛው ቆጣሪ ካለበት ስፍራ ወደ ማዕከል (አገልግሎት ሰጭው) ግንኙነት ማድረግ ያስችለዋል። በተመሳሳይ ከማዕከል ወደ ቆጣሪው መልዕክት መላክ የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህም በደንበኛው እና በአገልግሎት ሰጪው መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጾ ያበረክታል።

ሌላው ይህ ቆጣሪ የኃይል መቋረጥ ሲኖር መረጃ ይሰጣል። በኃይል ላይ ያለ የጥራት ችግር ካለ ያሳያል። በመተግበሪያው ምን ያህል ኃይል እየተጠቀመ እንደሆነ መከታተል ይቻላል። ፍጆታው እንዴት ነው የሚለውን ጉዳይ ማየት ይችላል። ወደ ፍጆታ ሂሳቡ ስንመጣም ለደንበኛው የሚሆን የሞባይል መተግበሪያ እያበለጸግን ነው። ይህም የደንበኞችንና የተቋሙን አሰራርና ተጠቃሚነት የሚያሳልጥ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር በነዳጅ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን በኤሌክትሪክ በሚሰሩ ለመተካት እየተሰራ ነው። ከዚህ አንጻር አሁን ላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ፍጆታ መሸከም የሚያስችል የመሰረተ ልማት አለ ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አሁን ላይ በሀገራችን አዳዲስ እና ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች፣ የንግድ ተቋማት እና ሕንጻዎች እየተገነቡ በመሆናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት እያደገ ነው። ለምሳሌ፣ ትናት በከተማችን ይታዩ የነበሩ ሕንጻዎች ትንሽ ኪሎ ዋት የሚጠቀሙ ነበሩ። አሁን ላይ በሜጋ ዋት የሚጠቀሙ ሆነዋል። በተጨማሪም በከተማችን በፊት የነበሩ ትንንሽ ቤቶች የነበሩበት ቦታ ላይ ትልቅ ሕጻንዎች እየተገነቡ ነው። እነኝህ ሕንጻዎች በውስጣቸው በርካታ ተቋማትን ይይዛሉ፤ ከፍተኛ የሆነ የኃይል አቅርቦትም ይፈልጋሉ።

የእነዚህን ሕንጻዎች የኃይል ፍላጎት ለማርካት እንደተቋም ብዙ ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግን ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልገሎት ዋና ፈተና ነው። ሆኖም መንግስት የመሰረተ ልማት አቅም ለማሳደግ በርካታ ቢሊዮን ብሮችን በመመደብ ከፍተኛ ስራዎችን እያከናወነ ነው።

ለእነዚህ ግዙፍ ተቋማት አገልግሎት ለመስጠት እንደ ሀገር በኃይል ማመንጨት በኩል በርካታ ስራዎችን እያከናወን ነው። በዚህ ዓመት የሕዳሴ ኃይል ወደ መስመር እየገባ ነው። በቀጣይም ሌሎች የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች (የእንፋሎት እና የነፋስ ) ማመንጫዎች ኃይል እየተገኘ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ የኃይል ፍላጎት ከ10፤ ከ20 ዓመት በኋላ የት ይደርሳል? ከዕድገቱ ጋር ተያይዞ ማስተናገድ የሚችል የመሰረተ ልማት አቅም ምን መሆን አለበት? የሚለውን ከግምት ውስጥ ያስገቡ እቅዶች እየተተገበሩ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የዋጋ ጭማሪ እንደሚደረግ እየተገለጸ ነው። የተደረገው የዋጋ ጭማሪ እንዴት የሚገለጽ ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ለምሳሌ፣ 27 ሳንቲም ሲከፍሉ የነበሩ ደንበኞች ከአራት ዓመት በኋላ አንድ ነጥብ አምስት ስድስት ሳንቲም ተጨማሪ የሚከፍሉ ይሆናል። አራት እጥፍ የሚባለው መነሻ ታሪፉ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ደንበኞቻችን ስለተደረገው ጭማሪ ፍትሃዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ሚዲያዎች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሊዘግቡ ይገባል።

እንደሚታወቀው የኃይል ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገቱ ቁልፍ መሳሪያ ነው። ለኢንዱስሪ፣ ለከተሞች፣ ለተለያዩ ልማታዊ ስራዎች አስፈላጊ ነው። ለኤሌክትሪክ ኃይል ማምረቻ የሚሆነው የመሰረተ ልማቱ ግንባታ እንደማንኛውም “ኮሜዲቲ” ይመረታል፤ ከፍተኛ ገንዘብም ይወጣበታል። ለምሳሌ፣ የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ለመስራት በመቶ ቢሊዮኖች ብር ወጭ ተደርጎበታል።

ይህ ኃይል ኢንዱስትሪዎች ጋር ሲደርስ ኢንዱስተሪዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ያደርጋል። ከቤታችን ሲገባ ሕይወትን ቀላል እንዲሆን ያስችላል። ነገር ግን ግድቦችን ለመስራት እና ኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ከፍተኛ ወጪ ይወጣል። ከግድቦች ጋር ተያይዘው ያሉት የኃይል ማመንጫ ጀኔሬተሮችና ተያያዥ ስራዎች፣ ኤሌክትሪክ ኃይል ከተመረተበት ደንበኛው ወዳለበት ትራንስፖርት ለማድረስ ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል።

እነዚህን ስራዎች ለመስራት እንደማኛውም ኢንቨስትመንት ብሮችን ተበድረን ነው ያለማነው ። ምክንያቱም ከሀገራችን ኦኮኖሚ አንጻር በአንድ ጊዜ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ማምጣት አይቻልም። በመሆኑም ፕሮጀክቶችን ለማከናወን ከውስጥም ከውጭም የሚወሰዱ ብድሮች አሉ። እነዚህ ብድሮች ደግሞ መመለስ አለባቸው። ብድሩ የሚመለሰው ደግሞ የተመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል በአግባቡ እና በትክክለኛ ዋጋ ሲሸጥ ነው። ይህም ማለት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ዋጋ ተብሎ የሚጠራው ነው።

አሁን የተሰራው የኤሌክትሪክ ታሪፍ የዋጋ ማመላከቻ ታሪፍ (coast reflective tariff) ነው። ይህም ማለት ያወጣውን ወጪ የሚተካ ወይም የሚመልስ ማለት ነው። ከወጣው ወጪ ተቋማችን ላይ ተጨማሪ ትርፍ የለውም ማለት ነው። መንግስት ትርፍ አልፈልግም ብሎ ለኢኮኖሚው መስዋት አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- የታሪፍ ማሻሻያው ለመሰረተ ልማቶች የወጣውን ብር ሙሉ በሙሉ መመለስ ያስችላል?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አይችልም። አሁን ለጊዜው እኛ ታሪፉን ሰርተናል፤ በየጊዜው ለውጦች ይኖራሉ። የዛሬ ስድስት ዓመት ማለትም በ2010 ዓ.ም የኢነርጂ ታሪፍ ለማስተካከያ ተፈቅዶ ነበር። ማስተካከያ የተፈቀደው 1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2010 ዓም ድረስ ምንም አይነት ማስተካከያ ባለመደረጉ ነው። በእነዚህ ዓመታት ተቋሙ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ተደራሽ ለማድረግ ለመሰረተ ልማቶች ከፍተኛ ገንዘብ ኢንቨስት ሲያደርግ ነበር። መሰረተ ልማቶች ደግሞ ሲሰሩ የነበረው በብድር ነው።

ነገር ግን ምንም አይት የዋጋ ማስተካከያ ባለመደረጉ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ ወጭ የተደረገው ብድር ለረጅም ጊዜ ተጠራቅሟል። እንደመስሪያ ቤት ዋናው ፈተናው የተጠራቀመው ብድር ነው ። በተለይ አሁን ላይ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከ300 ቢሊዮን ብር በላይ ያልተከፈለ ዕዳ አለበት። በ2010 ዓ.ም በተደረገው ማስተካካያ ብቻ ከቀጠልን ያወጣነው ወጪ መመለስ አንችልም። ይህ ደግሞ ነገ ሌላ ኃይል ማመንጫ መገንባት እንዳንችል ያደርጋል፤ ነገ ሌላ የማሰራጫ መስመር አይኖረንም፤ ምንም አይነት ስራ ሊከፈት የሚችልበት እድል አይኖርም። ስለዚህ እንዲህ አይነት ኢኮኖሚያዊ ችግር እንይዳከሰት መንግስት የወሰነው የዋጋ ማመላከቻ ታሪፍ ትክክለኛ እና ወቅቱን ያገናዘበ ነው።

በነገራችን ላይ የእኛን ታሪፍ ከሌሎች ሀገራት ጋር ስናወዳድር በጣም ዝቅተኛ ነው። ጎረቤታችን ኬንያ በአንድ ኪሎ ዋት 17 ብር ታስከፍላለች። እኛ ግን የዋጋ ማመላከቻ ብለን ያወጣነው ስድስት ብር ነው። ይህ በጣም ዝቅተኛ ነው። ሌሎች ከእኛ ሀገር ሶስት ዕጥፍ ይበልጣሉ።

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ተጠየቅ

# “የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከ300 ቢሊዮን …

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

ይህም ምን ያህል ዜጎች እንዳይጎዱ፤ ነገር ግን ተቋማቱ ደግሞ እንዳይሞቱ እና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ከፍተኛ ጥረት መደረጉን የሚያመላክት ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የተጨመረው የዋጋ ማመሳከቻ ታሪፍ የኑሮ ውድነትን ያባብሳል የሚል ስጋት አለ፤ ከዚህ አንጻር ምን ታስባል?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አሁን የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ በኑሮ ውድነት ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው የሚለውን ነገር ከፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመሆን አይተናል። ያን ያህል የጎላ ተጽዕኖ የለውም። የኃይል ታሪፍ መጨመሩ በሌሎች እቃዎች ላይ የሚያመጣው የዋጋ ጭማሪ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። የሚያመጣው ጫና ሁለት በመቶ ገደማ ነው። ይህም ከአራት ዓመት በኋላ ነው።

ይህ ታሪፍ በአንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ የሚጨመር ነው። ለምሳሌ 27 ሳንቲም ሲከፍሉ የነበሩ ደንበኞች መስከረም ላይ 35 ሳንቲም እንዲከፍሉ ነው የሚደረገው። ስለዚህ ከአራት ዓመት በኋላ ሰዎች የመክፈል አቅማቸው እያደገ ይመጣል። የዋጋ ማመላከቻ ዋጋው ስድስት ብር ቢሆንም ከታችኛው የኢኮኖሚ እርከን ላይ ያሉ ዜጎች የሚከፍሉት ግን ከዚያ ያነሰ ነው። ለምሳሌ፣ እስከ 50 ኪሎ ዋት ፓወር የሚጠቀሙት የሚከፍሉት ስድስት ብር ቢሆንም ከአራት ዓመት በኋላ የሚኖረው ጭማሪ አንድ ነጥብ ስድስት ብር ነው።

እስከ 70 ኪሎ ዋት 75 በመቶ ድጎማ አላቸው። እስከ 100 ኪሎዋት ያሉት 40 በመቶ እስከ 200 መቶ ኪሎ ዋት ተጠቃሚዎችም እንዲሁ ድጎማ አላቸው። ከዚያ በላይ ግን ተጠቃሚነቱ ሲጨምር የመክፈል አቅም አለው ማለት ነው። ጭማሪው ቀስ በቀስ እንዲሆን የተደረገው በአንድ ጊዜ በኅብረተሰቡ ሕይወት የሚያመጣውን ጫና ለመቀነስ ታስቦ ነው። ስለዚህ አሁን የተደረገው ጭማሪ ተጨመረ ተብሎ ሕብረተሰቡን ስጋት ውስጥ የሚከት አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ሕዳሴ ግድብ ኃይል አመንጭቶ ወደ ስራ በሚገባበት ወቅት ይህን ያህል ጭማሪ ማድረግ ተገቢነት የለውም የሚሉ የሕብረተሰብ ክፍች አሉ። በዚህ ላይ የእርሶ ምላሽ ምንድን ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ጭማሪው ያን ያል ሕብረተሰቡን በሚጎዳ መንገድ የተደረገ ነገር እንዳልሆነ ገልጫለሁ። ወደ ሕዳሴ ስንመጣ ግድቡን ለመገንባት የወጣ ገንዘብ አለ። ከ180 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ወጥቶበታል። ስለዚህ ይህን የወጣው ገንዘብ ካልተካነው ለሕዳሴ ግድብ የተበደርነው ብር ካልተከፈለ ተቋሙ እንዴት መቆም ይችላል? የተገነባው በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ወጭ ተደርጎበት ነው። ዜጎች ተሳትፈውበታል፤ በነጻ ገንዘባቸውን ለግሰዋል።

ይሁን እጂ አብዛኛው ገንዘብ ከሀገር ውስጥ ባንኮች በብድር የመጣ ነው። ለምሳሌ፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ አባላት ተባብረው አንድ ኩንታል ጤፍ ገዙ እንበልና እስከሚቀጥለው ወር መብላት ይችላሉ። ከሚቀጥለው ወር በኋላ ቤተሰቡ ሌላ ኩንታል ጤፍ መግዛት ካልቻለ መኖር አይችልም ማለት ነው። ስለዚህ ጤፉን ለመግዛት ሁሉም ጊዜውንና ጉልበቱን ሽጦ ብር ማምጣት መቻል አለባቸው። ይህም ልክ እንደዚህ ነው።

ዛሬ ሕዳሴን ገንብተናል፤ ነገ ደግሞ ሌላ መገንባት ካልቻልን ችግር ሊገጥመን ይችላል። ዋናው ተጠቃሚነቱ ላይ ነው። ሕዳሴን በዝቅተኛ ዋጋ ነው ተጠቃሚ እየሆን ያለው። ከኬንያ ብናመጣው ኖሮ ከኬንያ ለራሷ ዜጎች 17 ብር ከሸጠች ለእኛ በ17 አትሸጥም፤ ምንአልባትም 25 ብር ልትሸጥልን ትችል ነበር ። ሕዳሴ ነገም ጥገና ይፈልጋል፤ ለዚህ ደግሞ ገንዘብ መያዝ አስፈላጊ ነው። ሕዳሴ ባይመጣ ኖሮ በዚህ ዋጋ ኃይል ማግኘት አንችልም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የሰራው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት እንዳመላከተው በሀገር አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ አቅርቦቱ ከስትራቴጂክ እቅድ አንጻር 39 በመቶ ነበር። ከዚህ አንጻር የቀጣይ እቅዱ ምን ደረጃ ለማድረስ ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** እቅዶች በምናቅድበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ ሚታቀዱ ነገሮች ይኖራሉ። በእቅድ ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች ትክክል እና ተአማኒነት ባለው መንገድ ካላስቀመጥን እቅዱ ወረቀት ላይ ብቻ ይቀራል፤ ወይም ከአፈጻጸማችን በታች ይሆናል።

እንደ ተቋም አብዛኛው በተደራሽነት ላይ ያለው ፈተና የገንዘብ ውስንነት ነው። የውጭ ምንዛሬ እና የሀገር ውስጥ

**የእኛን ታሪፍ ከሌሎች ሀገራት ጋር ስናወዳድር በጣም ዝቅተኛ ነው። ጎረቤታችን ኬንያ በአንድ ኪሎ ዋት 17 ብር ታስከፍላለች። እኛ ግን የዋጋ ማመላከቻ ብለን ያወጣነው ስድስት ብር ነው። ይህ በጣም ዝቅተኛ ነው። ሌሎች ከእኛ ሀገር ሶስት ዕጥፍ ይበልጣሉ**

ገንዘብ በበቂ ሁኔታ ያለመኖር እቅዶቹ ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደረ ነው። አሁን ላይ በምናገኘው ገንዘብ ልክ እያቀድን ነው። ድሮ ግን አንድ ሺህ እና ሁለት ሺህ ከተሞችን እናገናኛለን በሚል ያለንን ያላማከለ እቅድ ይወጣ ነበር።

እንደ ሀገር ከተሞችን ተደራሽ ለማድረግ በፕሮግራም የተጀመረው 1998 ዓ.ም ነው። በዚያ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ኤሌክትሪክ የነበራቸው 690 ከተሞች ብቻ ነበሩ። በዚህ ፕሮግራም አዳዲስ ከተሞች እና መንደሮች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። አሁን ላይ 8 ሺህ 200 ከተሞች እና መንደሮች ኤሌክትሪክ እያገኙ ነው።

በ50 ዓመታት ውስጥ ተቋሙ ያልሰራውን ሁለት አስርት ዓመታት ባላሞላ ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት አንዳንድ ጊዜ የበጀት እና መሰል የአቅም ውስንነቶች ፈተና ናቸው ። ይህንና አሁን ላይ ከማክሮ ኢኮኖሚክ ሪፎርሙ ማሻሻያ ጋር ተያይዞ በዙ የተሻሻሉ ነገሮች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በዋና ኦዲተር ባለስልጣን እንደተረጋገጠው ተቋሙ የዓመቱ የፊዚካል የስራ አፈጻጸም ዝቅተኛ ሆኖ ሳለ የሚጠየቀው በጀት ግን ከተቀመጠው በላይ ነው። በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አዎ! አንዳንድ ጊዜ ቀጣይነት ያላቸው ፕሮጀክቶች ይኖራሉ። በዚህ ወቅት ፊዚካል እቅድ እና ፋይናንሻል እቅድ በትክክል ላይመጣጠኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ባለፈው ዓመት ሰኔ እና ግንቦት ላይ ስናከናውናቸው የነበሩት የፕሮጀክት ክፍያዎች በዚህ በጀት ዓመት ላይጠናቀቁ ይችላሉ። አጋጣሚ ሆኖ ኦዲተሮች ደግሞ በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ሊያርጉ ይችላሉ። በዚህ ወቅት የፊዚካል የስራ አፈጻጸም ዝቅተኛ ሆኖ የተጠቀምነው በጀት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የተዛባ ግንዛቤ (misperceive) እንዳይደረግ እና ገንዘብ እያባከኑ ነው ወደ ሚለው ትርጓሜ እንዳይመጣ ፕሮጀክቶች ሁል ጊዜ በገንዘብ የተወሰኑ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። የፊዚካል አጠቃላይ ስራቸው በዚህን ያህል በጀት ነው የሚጠናቀቁት ከተባለ ያ አይቀየርም። ምን አልባት የዋጋ ማስተካከያ ከሌለ በስተቀር አይቀየርም፤ የሚባክን ገንዘብም አይኖርም። ስለዚህ የተለየ ነገር ካልሆነ በስተቀር ኮንትራክተሩ በያዘው ዕቅድ ስለሚሄድ ብዙ ችግሮች አይኖሩም።

**አዲስ ዘመን፡- ከፍተኛ ወጭ የወጣባቸው ማስተሳሰፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ተሰርተው እያለ ተቋማችሁ መስራት ያለበትን ባለመስራቱ የገጠር አካባቢዎች መብራት እያገኙ አይደለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ይህ የሆነበት ምክንያት የማስተላለፊያ መስመሮች እና የማሰራጫ ጣቢያ ሁለት ፕሮጀክቶች የሚሰሩት በተለያዩ ኮንትራክተሮች በመሆኑ ነው። ማስተላለፊያዎችን እና ማሰራጫዎችን የሚሰራው ኮንትራክተር አንድ ካልሆነ እና ሁለቱ ፕሮጀክቶች በአንድ ጊዜ ካላለቁ/ካልተጠናቀቁ ወይንም አንደኛው ፕሮጀክት የሚዘገይ ከሆነ የጠቀሳችሁትን አይነት ችግር ሊከሰት ይችላል። ስለሆነም እስከሚጠናቀቅ ሊጠብቁ ይችላሉ ማለት ነው። ይህም ማቀናጀትን ይጠይቃል። ለማቀናጀት የሚከብደው ደግሞ አንዱ ጥሩ ሲሰራ ሌላኛው ኮንትራክተር ላይሰራ ይችላል።

**አዲስ ዘመን ፡- በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ስራ ላይ የሚገኙ የተቋማችሁ ሰራተኞች ምን አይነት የደህንነት ዋስትና ጥበቃ ታደርጋላችሁ? አደጋ በደረሰ ጊዜ የሕይወት ኢንሹራንስ አላችሁ?**

**አቶ ሽፈራው ፡-** እንግዲህ ሁሉም ሰው ወደስራ ሲወጣ የሚተማመነው የሀገሪቷን ፀጥታ ኃይል ነው። እኛም አሁን ከቤታችን ወጥተን ቢሮ ስንመጣ ሀገሪቷ ያለው የፀጥታ አካል ይጠብቀናል በሚል እሳቤ ነው። ነገር ግን እዚህ አዲስ አበባ ራሱ አንዳንድ ጊዜ ከዛ ውጪ የሆኑ ገጠመኞች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። በተመሳሳይ በተቋማችን ሰራተኞች ላይ እንደዚህ አይነት ነገሮች ያጋጥማሉ።

ግን በጣም ውስን ችግር ነው። ችግሮች ሲያጋጥሙ ተቋሙ ለሰራተኞቹ ኢንሹራሽ አለው። ከተጎዱ የሚያሳክምበትም አሰራር አለው። በአካል ጉዳት ከደረሰም ለዚያ ኢንሹራንስ የሚከፈልበት አሰራር አለ። በሕይወትም ደግሞ የሚከሰት አደጋ ካለ በተመሳሳይ ኢንሹራንስ አለው።

በጸጥታ ችግር የመሰረተ ልማቶች ጉዳት ከደረሰባቸው ኃይል የተቋረጡባቸውን አካባቢዎች ለመጠገን የሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያስችል የጸጥታ መዋቅር በቦታው ሲኖር ጥገናው ይከናወናል። ለምሳሌ መከላከያ አከባቢዎችን ከተቆጣጠረ እና ለስራው የጸጥታ ሁኔታውን ዝግጁ ካደረገ በኋላ ከስር ከስር ተከታትለን ገብተን እንጠግናለን።

**አዲስ ዘመን ፡- የደንበኞችን ወረፋ ለማስቀረት በካርድ የሚሰሩ ማሽኖችን ከመጠቀም አንጻር ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አሁን ላይ ለደንበኞች ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረግን ነው። አገልግሎት ፈልገው ወረፋ የሚጠብቁ ደንበኞችን ችግር ለመፍታት «ቤንዲንግ» ማሽን አዘጋጅተናል፤ ፖስ ማሽንም አምጥተናል። በዚህም አገልግሎት እያገኙ ነው። ከዚህ ባሻገር አገልግሎት የምንሰጥበትንም ጊዜ ጨምረናል።

**አዲስ ዘመን ፡- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚስተዋለው የሰላም መደፍረስ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የፈጠረውን ጫና እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ሽፈራው፡-** መሰረት ልማት ላይ ከባድ ጫና ይፈጥራል። የሰላም መደፍረሱ በሌሎች ዘርፎች ላይ የሚመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ በተመሳሳይ በእኛም ላይ ተጽዕኖ ያመጣል። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የመከላከያ ሰራዊት ብዙዎችን አካባቢዎች አረጋግቷል። በምዕራብ ኢትዮጵያ አገልግሎት ተቋርጦባቸው የነበሩ አካባቢዎች አሁን ላይ ወደ አገልግሎት እየተመለሱ ነው። ወደ 360 የሚሆኑ መንደሮች ኤሌክትሪክ ተቋርጦባቸው ነበር።

መከላከያና ሕብረተሰቡ እየረዳን እኛም ሰራተኞችን ልከን ዜጎች ወደ ነበሩበት ሰላማዊ የኑሮ እንቅስቃሴ እንዲመለሱ የበኩላችንን አስተዋጽኦ እያደረግን ነው። በዚህም ከ300 በላይ ለሚሆኑት አገልግሎቱን መልሰናል። የተወሰኑ ይቀሩናል፤ በሚቀጥለው ወር እንጨርሳለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን ፡- ስርቆትን ለመከላከል ከፀጥታ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ከመስራት አንጻር ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ስርቆትን ለመከላከል ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በጋራ እየሰራን ነው። የእኛ መሰረተ ልማት ያለው በየሰው ደጅ ነው። ስለሆነም ዋናውና ትልቁ ኃላፊነት የሕብረተሰቡ ነው። ሀብቱ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አይደለም፤ የመንግስትም አይደለም! የሕዝብ ነው። ይህን ሀብት ሕብረተሰቡ ሀብቴ ነው ብሎ መጠበቅ አለበት። ስለዚህ ሕብረተሰቡ እና በየአካባቢው የሚገኙ አስተዳደር አካላት ይሄንን መሰረተ ልማት እንዲጠብቁ ግንዛቤ ለመፍጠር እየተሰራ ነው።

አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሕብረተሰቡ በባለቤትነት ስሜት በመጠበቅ ሌቦችን እጅ ከፍንጅ ይዞ ለጸታ ኃይል አስረክቧል። በጥቆማ ተይዞ በፍትህ አካላት እርምጃ የተወሰደባቸው አሉ። ይህንን ማድረግ የሁላችንም ነው። የሚዲያው ድርሻም ግንዛቤ ከመፍጠር አንፃር ስራዎችን መስራት አለበት።

እዚህ ሰፈር ያለው ሕዝብ ኤሌክትሪክ ባያገኝም እንኳን የኤሌክትሪክ መስመሩ በሰፈሩ ካለፈ ነገ ተጠቃሚ እንደሚሆን ሊገነዘብ ይገባል። ለዚህ ያን መሰረተ ልማት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት። ነገር ግን መሰረተ ልማቱ ከፈረሰና ከተሰረቀ አገልግሎት የማግኘት እድሉ እየራቀ ይሄዳል፤ እያገኙ ያሉትም ይቋረጥባቸዋል። ስለዚህ ይህ እንዳይሆን የጋራ ንብረታችንን በጋራ መጠበቅ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ስሀገር ውስጥ ተቋራጮች የሚሰጠው ውል አቅማቸውን ያላገናዘበ እና የሚደረገው ቁጥጥርም ልል መሆኑ በዋና ኦዲተር ከቀረበው ሪፖርት ማየት ተችሏልና በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ልክ ነው፤ የአቅም ውስንነት ሊኖር ይችላል። እኛ በኢትዮጵያ ውስጥ እየሰራን ያለነው አንዱ ስራ ሕብረተሰቡ ቀጥታ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው። ሌላው ደግሞ ዜጎች በዚህ ዙሪያ ላይ የስራ እድል እንዲያገኙ ነው። ቀደም ሲል በውጭ ኮንትራክተሮች ሲሰሩ የነበሩት ስራዎች ቀስ በቀስ በሀገር ውስጥ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው። ያንንም ስልጠና በመስጠት ጭምር፤ አቅም እንዲፈጥሩ በማገዝ የተሰራ ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ ግን መውደቅ እና መነሳት ሊኖር ስለሚችል እየተከታተሉ እያረሙ መስመር ውስጥ እያስገቡ መሄድ ተገቢ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በምትፈልገው ደረጃ የማያድጉ እና የማይለወጡ አሉ። እነሱን ደግሞ በማስተካከል አቅም መፍጠር እንዲችል ማገዝ፤ በሚገባቸው ጊዜ አቅም መፍጠር ካልቻለ ደግሞ ማስወጣት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዋናነት ለፕሮጀክቶቻችሁ የጨረታ መስፈርታችሁ ምንድን ነው?**

**አቶ ሽራው፡-** የጨረታ መስፈርታችን ጥራት ነው። እንደ ውጭ ኮንትራክተሮች በጣም የተጋነነ አይነት የጥራት መስፈርት ብናወጣ አያሟሉም። የስራ ጥራትንም ጉዳይ ደግሞ አገልግሎቱ ላይ ተፅዕኖ ስለሚያመጣ በመሆኑ የምንታገሰው አይደለም። ይህን ከግምት በማስገባት ተጫራቾች በትንሹ ሊኖራቸው የሚችለው የቴክኒካል እና የፋይናንስ አቅም ምንድን ነው? የሚለው አስቀምጠን በዚያ እንገመግማለን ።

ከዚህ አንጻር አንዳንዶች ከመስፈርቱ ጋር አቻ በሆነ መልኩ ሚጣጣም አቅማቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ገንዘብ ይገኝበታል በሚል በግርግር ወደ ጨረታ የሚመጡ አሉ። እነሱ በሂደት ከውስጡ እየጠሩ ይሄዳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ዋና ኦዲተር ካስቀመጠው የአይቲ እና የፋይናንሻል ኦዲት በመነሳት ስትራቴጅክ እቅዶችን ከመተግበር አኳያ ምን እያደረጋችሁ ነው? አሰራራችሁን ለማዘመን እንዲረዳ የአይሲቲ ኦዲት አሰርታችሁ ታውቃላችሁ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** እንደተቋም የአይሲቲ ኦዲት እናደርጋለን። እንደማንኛም «ፐርፎርማንስ» ኦዲት የአይሲቲ ኦዲት እናደርጋለን። ራሳችንም እንዴት ነው አይሲቲን እየተጠቀምን ያለነው? የሚለውን በባለሙያዎች የዳሰሳ ጥናት እያየን ነው። በዚያ ላይ ተመስርተን ተጨማሪ ማሟላት እና ማጠናከር ያለብን አካባቢዎችን በመለየት በእሱ ላይ እንሰራለን። የአይሲቲ አጠቃቀማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው። በ2012 ዓ.ም የገቢያችን አሰራር ወደ አይሲቲ ለውጠናል። አቅሙ ቀስ በቀስ እያደገ ነው።

ነገር ግን አሁንም በተፈለገበት ደረጃ ላይ አይደለም። የውስጥ አቅምን እንዴት እናሳድጋለን የሚለውን ከሚያለሙ አካላት ጋር እየተነጋገርን ነው። እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ ተቋማትን ተሞክሮ አይተናል። በቀጣይም ከተሞክሮዎች በመነሳት ማስተካከያዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዳሴ ግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ ነው፤ ይሄም የሀገሪቱን ሕዝቦች የኃይል ፍላጎት ለማዳረስ የሚያስችል ይሆናል፤ ታዲያ የመሰረተ ልማቱ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሽፈራው፡-** መሰረተ ልማት ለኃይል አቅርቦት ወሳኝ ነው። ስለሆነም ሕዳሴ ላይ ያለውን ኃይል ማጓጓዝ ከዚያ ደግሞ ደንበኛውና ኢኮኖሚው ጋር በማድረስ መስራት ያለባቸው ስራዎች ናቸው። ይህም በቀጣይት የኢኮኖሚ እድገቱን ተከትሎ የሚሰራ ነው። ለዚያም የሚያስፈልጉ ኢንቨስትመንት ስራዎችን ማከናወን ይጠይቃል። ለዚህ መሰረተ ልማት ግባታም 545 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከዓለም ባንክ የተገኘ ብድር አለ።

አሁን ያለውን የኃይል ፍላጎት የሚያሟላ መሰረተ ልማት እየተገነባ ነው። ነገር ግን ፍላጎት የሚቆም ሳይሆን የሚቀጥል በመሆኑ የማስፋፋት ስራዎችን እንቀጥላለን። ስለዚህ ሕዳሴም አሁን ሲገነባ እንጠቀምበታለን ተብሎ የሚሰራ ነው። ስለዚህ በማክሮ ኢኮኖሚ የሚፈቱ ብዙ ማነቆዎች አሉ። የውጭ ምንዛሬ ላይ ያለው እጥረት ይህ እቅድ ይፈታዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ሽፈራው ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# "የበለፀገች ኢትዮጵያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመሆኑ፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች፣ ከተሞችና የፌዴራል ተቋማት ያለው ከፍተኛ አመራር በተመሳሳይ የፓርቲው ተልዕኮዎች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመያዝ ለተሻለ ውጤት እንደሚያተጋው አብራርተዋል።

መሪነት ራስን መስጠትን፣ ሆደሰፊነትንና ዓላማን የማሳካት ቁርጠኝነትን እንደሚጠይቅ ጠቁመው፣ ከፍተኛ አመራሩ የወሰደው ሥልጠናም የመሪነት ቁልፍ መርሆዎችና ባሕሪያትን በአግባቡ እንዲገነዘብ ያደረገ በመሆኑ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ ለማስመዝገብ አቅም ይፈጥራል ሲሉ ገልጸዋል።

በሥልጠናው ሕልምንና ትልምን ለማሳካት የሚያግዙ እይታዎችና የመፈፀሚያ ትርክቶች ላይ ያተኮሩ ሀሳቦች፣ በሕዝብ ቅቡልነትና ትብብር የመሥራት አቅም፣ እውቀት መር ሽግግርን ለማፅናት የሚያስፈልጉ ሰብዕናዎች ላይ የመሥራትና የፀጥታ ችግሮችን ወደ ተሟላ ሠላም የሚያሻግሩ ሂደቶችና የአመራር ሥነምግባርን በሚመለከቱና ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጽሑፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

# በክልሉ የሚንቀሳቀሱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ አሳሰበ፡፡

የቢሮው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ቢያዝን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በክልሉ ለመመዝገብ ከታቀደው 7 ሚሊዮን ተማሪዎች ውስጥ ከአራት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት አልተመዘገቡም፡፡

ከነሐሴ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የተማሪዎች ምዝገባ እየተካሄደ ይገኛል ያሉት አቶ ጌታቸው፤ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ነባርም ሆነ አዲስ ተማሪዎች ምዝገባ እንዲያካሂዱ ለማድረግ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ እስካሁን የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ካለፉት ዓመታት አንጻር ሲታይ ግን ዝቅተኛ ነው ብለዋል፡፡

ከመስከረም 7 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮም በክልሉ የመማር ማስተማር ሥራው ተጀምሯል ያሉት ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል እንዲመዘገቡ ከሚጠበቁ ተማሪዎች 27 በመቶ የሚሆኑ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ወደ 20 በመቶ የሚጠጉ ተማሪዎች ብቻ መመዝገባቸውን ጠቁመዋል፡፡ ምዝገባው አሁንም በመካሄድ ላይ በመሆኑ ቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል የሚል ተስፋ መኖሩን ገልጸዋል።

በክልሉ ያለው የፀጥታ ችግር ሁኔታ ተማሪዎች በሚፈለገው ልክ እንዳይመዘገቡ ማድረጉን ጠቁመው፤ የመማር ማስተማር ሥራዎች በአግባቡ አለመካሄድ ትውልዱ ላይ ከፍተኛ ስብራት የሚፈጥር ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎችም ትምህርት ከየትኛውም ፖለቲካ ጋር የማይገናኝና ትውልድ የሚቀረጽበት መሆኑን በመገንዘብ የመማር ማስተማር ሥራውን ከማደናቀፍ ሊታቀቡ ይገባል ብለዋል፡፡

ትምህርት ትውልድ የሚቀረጽበት ሂደት ነው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ትምህርት ቤቶችም ዜጎችን ለመቅረጽ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሄደው እንዲመዘገቡና ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

በክልሉ ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት ባለፈው ዓመት ከ4 ሺህ በላይ የትምህርት ተቋማት ተዘግተው መከረማቸውን ያመለከቱት አቶ ጌታቸው፤ በዚህም ከ2 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ተለይተው ቆይተዋል፡፡ 12ኛ ክፍል መፈተን የነበረባቸው ተማሪዎችም ሳይፈተኑ ቀርተዋል ብለዋል፡፡

ይህ ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎችና ወላጆች ላይ የሚፈጥረው የሥነ ልቦና እና በአጠቃላይ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ስለሆነ ይህን ሁኔታ ለመቀየር መረባረብ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ቢሮው አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማቅረብና የመማር ማስተማር ሥራው በአግባቡ እንዲካሄድ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን አስታውሰው፤ ከተፅዕኖ ባለፈ ግን ተማሪዎች ከመስቀል በኋላ ወደ ትምህርት ቤት የመምጣት ልምድ መኖሩም በተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ላይ የራሱን አሉታዊ አስተዋፅዖ አበርክቷል ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

ስለሆነም ከማኅበረሰቡ ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አወንታዊ ሚናቸውን እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

# ምርታማነት ላይ የተደቀነው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በግብርናው ዘርፍ ላይ ትልቅ ስጋት ደቅኗል፤ ከአራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በከፍተኛ አሲዳማነት ተጠቅቷል፡፡ በከፍተኛ አሲዳማነት ከተጠቃው አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አንድ ሚሊዮን ሄክታሩ ምንም አይነት ምርት አይሰጥም፡፡

ምርት እየሰጠ ያለው መሬት በዝቅተኛ፤ በመካከለኛና በከፍተኛ አሲዳማነት እየተጠቃ ነው፤ በአጠቃላይም 12 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዝቅተኛ፣ በመካከለኛ፣ በከፍተኛ የአሲድ መጠን ተጠቅቷል፡፡ ይህም በግብርናው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ስጋት ደቅኗል፡፡

የአፈር አሲዳማነት በማከም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እየተሠራ ቢሆንም እስካሁን በአሲዳማነት ከተጠቃው 43 በመቶ መሬት ውስጥ 140 ሺህ ሄክታር ብቻ ነው የታከመው፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ሥራ አስፈፃሚ ፋኖሴ መኮንን ለኢፕድ በሰጡት አስተያየት፤ የአፈር አሲዳማነት በኢትዮጵያ ግብርና ምርትና ምርታማነት ትልቅ ስጋት ሆኗል፤ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በከፍተኛ አሲዳማነት ተጠቅቷል፤ በከፍተኛ አሲዳማነት ከተጠቃው አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አንድ ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው ምርት ከመስጠት ሙሉ በሙሉ ወደ አለመስጠት ተሸጋግሯል፡፡

በኢትዮጵያ ለእርሻ አገልግሎት የሚውለው መሬት በከፍተኛ ዝናብ ጥርጊያ፣ በአፈር መሸርሸር፤ የሰብል ቅሪትን ሙሉ በሙሉ በማንሳት አፈሩ በከፍተኛ ሁኔታ ለአሲዳማነት እየተጋለጠ ነው፡፡ በየዓመቱ የአሲዳማነት መጠን ዝቀተኛ የነበረው አፈር ወደ መካከለኛ፤ መካከለኛው ወደ ከፍተኛ እያደገ ነው፤ በዝቅተኛ፣ በመካከለኛ፤ በከፍተኛ የአሲዳማነት መጠን የተጠቃው በአጠቃላይ 12 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ይሆናል፡፡ ይህም በሌሎች ሀገራት አንድ ራሷን የቻለች ሀገር የሚያህል ነው ይላሉ፡፡

በአፈር ውስጥ ያሉት "ካታላይኖች"ና ለተፈጥሮ ሀብት ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮች እንደ ካልሲየም፤ ማግኒዚየም፣ ፖታሽየም የመሳሰሉ ማዕድናት በዝናብ ውሀ በመታጠብ በአፈር ውስጥ የናይትሮጂን፣ የአልሙኒየም ንጥረ ነገር እየበዛ ሲመጣ አፈሩ አሲዳማ ይሆናል፡፡ አሲዳማ የሆነ አፈር የሰብል እድገትን በማቀጨጭ ሙሉ ለሙሉ ምርት እንዳይሰጥ ያደርጋል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የአፈር አሲዳማነት የሰብሎችን ስር ያቃጥላል፤ እድገታቸውን ይጎዳል፤ አየርና ውሀ ከመሬት ስር ለመውሰድ እንዲቸገሩ ያደርጋል፤ ለሰብሎች የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮችን የሚያብላሉ ማይክሮ ኦርጋኒዝሞች ሥራ ላይ እንዳይውሉና ለአዝርዕቶች እድገት የሚጠቅመው የፎስፎረስ ንጥረ ነገር እንዳይደርስ ያደርጋል፤ የአፈር ማዳበሪያ 70 በመቶ ጥቅም ላይ እንዳይውል በማድረግ የሀገርን ግብርናና ኢኮኖሚ እየጎዳ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በምዕራብ ኢትዮጵያ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ በተለይ መንዲ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ምሥራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ በአዊ ዞን፤ በደቡብ ጎንደር፣ ቤንሻንጉል ክልል አሶሳ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሲዳማ አካባቢ ከፍተኛ በአሲዳማነት የተጠቃ አፈር እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ለግብርናው ዘርፍ ስጋት የሆነውን የአፈር አሲዳማነት የአፈርና የውሃ ጥበቃ በመሥራት የመከላከልና የተጠቃውን በግብርና ኖራ የማከም ሥራ እየተሠራ ነው፤ አንድ ሄክታር መሬትም በአማካኝ 30 ኩንታል የግብርና ኖራ ይፈጃል፤ በግብርና ኖራ የታከመ መሬትም ከአራት እስከ ስድስት ዓመት ከፍተኛ ምርት ይሰጣል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር በአፈር ሀብት ልማት የአፈር ጤንነትና ልማት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ ሙሉጌታ አበራ በበኩላቸው፤ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ባለባቸው አካባቢዎች የአፈር አሲዳማነት እየተስፋፋ ነው፡፡

በ1989 ዓ.ም በተጠና ጥናት በኢትዮጵያ ለአፈር አሲዳማነት የተጋለጠው የመሬት ከፍል 40 በመቶ ነበር፤ አሁን 43 በመቶ ሆኗል። ባለፉት 27 ዓመታት የአፈር አሲዳማነት ሦስት በመቶ ጨምሯል፤ ሦስት በመቶ የሚታረስ መሬት ብዙ ነው፤ ቀላል የሚባል አይደለም፤ የአፈር አሲዳማነት ለምርትና ለምርታማነት ትልቅ ስጋት መሆኑንም ያሳያል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በተጨማሪም በ2014 ዓ.ም በተሠራ ሀገር አቀፍ ጥናት ሦስት ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት አሲዳማ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬትም በመካከለኛ አሲዳማነት መጠን እንደተጠቃ ጥናቱ አረጋግጧል ብለዋል።

በሀገሪቱ ከፍተኛ ዝናብ አፈሩ መሸርሸሩ፤ የማሳ ተረፈ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ማንሳት የአፈር አሲዳማነትን ሽፋን እየጨመረ ነው፤ ከዓመት ዓመት እየጨመረ የመጣው የአፈር አሲዳማነት ለምርታማነት ስጋት እየሆነ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

በአሲዳማነት የተጠቃ መሬት የአፈር ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር መጠቀም ቢቻልም ምርት አይሰጥም፤ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ በመሥራት፤ የተጠቃውንም በግብርና ኖሯ በማከም ከ50 እስከ 100 ፐርሰንት ምርት እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለውም ሥራ ከ2006 እስከ አሁን ማለትም ከ2016 ዓ.ም አንድ መቶ 40ሺህ ሄክታር መሬት በግብርና ኖራ ታክሟል ሲሉ ተናግረዋል።

የአፈር አሲዳማነትን በመከላከል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የአፈር ማዳበሪያን በጥናት የመጠቀም፤ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ መሥራት፤ የሰብሎችን ቅሬት ማሳው ላይ እንዲቀሩ የማድረግ፤ ወደ አሲዳማነት የተቀየረውን መሬት በግብርና ኖራ የማከም፤ ችግሩንም በዘላቂነት ለመፍታት የተፈጥሮን ማዳበሪያ የመጠቀም ሥራ እየተሠራ ነው ይላሉ።

በግብርና ኖራ የታከመ አሲዳማ አፈር በከፍተኛ ሁኔታ እስከ ስድስት ዓመት ምርት ይሰጣል፤ በ2017 ዓ.ም ሦስት መቶ ሺህ ሄክታር መሬት ለማከም እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# ኢሬቻ - የኅብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ



ፎቶ፡- ኢዮብ ተፈሪ

ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢሬቻ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ፈጣሪን(ዋቃ) ለማመስገን፣ ለመለመን ተሰባስቦ የሚወጣበት የምስጋና በዓል ነው፡፡

ኦሮሞ ባሕሉን፣ ቋንቋውን፣ ማንነቱን፣ የሚያንፀባርቅበት የራሱ የሆነ የገዳ ሥርዓት ያለው ሕዝብ ነው ያሉት ተመራማሪው፣ ኢሬቻ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ከሚያንፀባርቁ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻ በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠራ ሲሆን በቱለማዎች ኢሬቻ፣ በመጫዎች ኢሬስ፣ በሐረርጌ ኢሬሳ፣ እንደሚባልና ሌሎች ስያሜዎችም እንዳሉት ጠቅሰው፣ በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራ እንጂ የሚፈጸመው ሥርዓት ግን አንድ አይነት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ በምሥጋና፣ በጸሎት ፈጣሪን (ዋቃ) ለመለመን፣ ለማመስገን ተሰባስቦ የሚወጣበት መሆኑን በመግለጽ፣ በዓሉ የኦሮሞ ሕዝብ ለምሥጋና በፈጣሪ ፊት የሚቀርብበት እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

ኢሬቻ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚካሄድ ቢሆንም በዋናነት በሁለት ኢሬፈናዎች እንደሚከበር ገልጸው፣ እነዚህም ኢሬቻ ቱሉና ኢሬቻ መልካ ተብለው ይጠራሉ ሲሉ አቶ ጌታቸው ይናገራሉ፡፡

ሕዝቡ ከቀበሌው ከመንደሩ ጀምሮ በአካባቢው በሚገኙ መልካዎች ላይ ተገኝቶ ኢሬፈና ያካሂዳል ያሉት ተመራማሪው፣ በመስከረም ወር አንድ ቦታ ላይ ተሰብስበው የሚያከብሩት ትልቁ ኢሬቻ በዓል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የክረምቱን ጨለማ፣ ጭቃ፣ ዝናብ አውጥቶ ለመስከረም አደይ ያሸጋገረውንና እርጥበትን ለሰጠ ፈጣሪ (ዋቃ) ምስጋና እንደሚቀርብ ጠቅሰው፣ ከፊታችን ያለው ጊዜ ብርሃን ነው በማለት አበባና እርጥብ ሣር በመያዝ ለምስጋና ወደ መልካ እንደሚወጣ ይገልጻሉ፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ እርጥብ ሣር፣ አበባ ይዞ ለምስጋና ወደ መልካ ሲወጣ የተለያዩ ትርጓሜዎች ሲሰጡ እንደሚስተዋል በመግለጽ፣ ነገር ግን ኢሬቻ በአንድነት ሆኖ ፈጣሪውን (ዋቃ) የሚያመሰግንበት፣ የሚገናኝበት፣ የሚወያይበት፣ ባሕሉን የሚያንፀባርቅበት፣ የእርቅ፣ የአንድነት የሠላም የምስጋና በዓል ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ኢሬቻ ከኦሮሞ ሕዝብ አልፎ በሀገሪቱ በሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችም ዘንድ በድምቀት የሚጠበቅ በዓል መሆኑን ገልጸው፣ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በደስታ መጥተው የሚሳተፉበትና የርስ በርስ ትስስር የሚፈጠርበት እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

በኢሬቻ ዙሪያ የብሔር ብሔረሰቦች አመለካከት እየተቀየረ መጥቷል የሚሉት አቶ ጌታቸው፣ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን የሚፈጥር፣ የአንድነት፣ የፍቅር፣ ሠላም አስፋኝ መሆኑን ተረድተዋል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻ ሠላም፣ እርቅ፣ ፍቅር፣ መረጋጋት የሚፈጠርበት ቦታ በመሆኑ ከጥንት ጀምሮ ኢሬፈና ሲካሄድ የመጣ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢሬቻ ቱሉና መልካ ከኦሮሞ ሕዝብ አኗኗር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ኢሬቻ በውስጡ ከሚገኙ እሴቶች መካከል ግንኙነት ለመፍጠር፣ ሀገራዊ አንድነትን ለማምጣት፣ እርቅ ለማውረድ፣ ሠላምን ለማምጣት ከፍተኛ ቦታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

በዓሉ እስካሁን ከተደረገበት ጥናትና ምርምር ባሻገር ለሀገር ጥቅም ላይ መዋል በሚችል መልኩ ሊሠራበት እንደሚገባ በመግለጽ፣ ኢሬቻን ለዓለም በማስተዋወቅ ረገድም ምሑራን፣ ሚዲያ፣ የኦሮሞ ሕዝብና መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም የበኩላቸውን መወጣት እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻ እርጥብ ሳር በመያዝ ፈጣሪ (ዋቃ) የሰጠውን ስጦታ የሚመሰገንበት ነው የሚሉት ደግሞ በጂማ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ሥነጽሑፍ ፎክሎር መምህር ደረጄ ፋፋ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

ኦሮሞች በኢሬቻ ከክረምት ወደ መስከረም(ቢራ) ላሸጋገረው ፈጣሪ (ዋቃ) ነው በማለት ያመሰግናሉ ያሉት ደረጄ (ዶ/ር)፣ ሠላም፣ አንድነትን፣ አብሮ መኖርን አድለን በማለት ይለምናሉ ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻ ካሉት ጠቀሜታዎች መካከል ሠላምን ማውረድ፣ እርቅን ማምጣት፣ አብሮነትን፣ አንድነትን የሚፈጥር መሆኑን ጠቅሰው፣ ባሕሉን፣ ሥርዓቱን፣ እሴቱን፣ ሕጉን በጠበቀ መልኩ በኢሬቻ ሠላምን ማውረድ፣ አንድነትን ማምጣት የሚቻልባቸው ጉዳዮች ሊታወቁ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

የኢሬቻን የአንድነት፣ ሠላም፣ የመተሳሰብ፣ እሴትና ባሕሉን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ በዓመት ተሰብስቦ ማክበር ብቻ ሳይሆን የኢሬቻ እሴት የሆኑትን አንድነትን፣ ሠላምን በማውረድ በጋራ መኖር እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡

ኢሬቻ እንዴት ጀመረ፣ ከምን ተጀመረ፣ እንዴት መቀጠል አለበት፤ የሚለውን በትክክል ጥናት ሊደረግበት እንደሚገባ የገለጹት ደረጄ (ዶ/ር)፣ ኢሬቻ የሠላም፣ የአንድነት በዓል መሆኑ ከመሠረቱ ጀምሮ በትክክል ተጠንቶ ሕዝቡን ማስገንዘብ እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡

ኢሬቻን የኦሮሞ ብቻ አድርጎ ማየት ተገቢ እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ በኢሬቻ ሠላም፣ ምሥጋና፣ አንድነት የሚሰበክበት በመሆኑ ጉዳዩ የጋራ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የኢሬቻን ሥርዓቱ፣ እሴቱን፣ የፈጣሪንና ፍጡርን ሕጎች ማወቅና ማክበር፣ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ ይህን ማድረግ ሲቻል ሠላም፣ አንድነት፣ መግባባትን፣ መቀራረብን መፍጠር እንደሚችል ያስረዳሉ።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# በአቅርቦትና ውድድር የተፈታው የደብተር ዋጋ ንረትና ስጋት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱን ዓመት በተቀበልንበት በኢትዮጵያውያን የዘመን መለወጫ ወርሃ መስከረም ላይ እንገኛለን።የወራቶች ንጉስ የሆነውና በተለያዩ በዓላት የሚታጀበው ይህ ወር ከፍተኛ ወጪ ይጠየቅበታል። መስከረም አንድ ቀን የሚከበረውን አዲስ ዓመት ተከትሎ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የዘመን መለዋጫ በአላት፣ የመስቀል ደመራና የኢሬቻ በዓላት ደግሞ ይመጣሉ።

ለበዓላቱ ማክበሪያና ማድመቂያ የተለያዩ ወጪዎች ይደረጋሉ። የእነዚህ ተከታታይ በዓላት መከበር ግድ የማይሰጠው ትምህርት ቤትም እንዲሁ በወርሃ መስከረም የመጀመሪያ ሳምንት የሚከፈት በመሆኑ ሌላው ተጨማሪ ወጪን የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት በሚዳጉበት በዚህ ወቅት የትምህርት ቁሳቁስ መግዛት የግድ ነው። እኛም በዕለቱ ዝግጅታችን ለተማሪዎች አስፈላጊና የግድ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁስ ዋጋ ምንና አቅርቦቱ ምን ይመስላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይዘን የገበያ ቅኝት ለማድረግ መርካቶ ገበያ ዘልቀናል።

ገበያው በትምህርት ቁሳቁስ ተሞልቷል። የደብተር መያዣ ቦርሳን ጨምሮ የምሳ ዕቃ፣ የተማሪዎች የውሃ ኮዳ፣ ደብተር፣ እስኪሪብቶ፣ እርሳስና መቅረጫ፣ ላጲስ፣ ከለርና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁስ ገበያውን ሞልተውታል፡፡

የ2017 የትምህርት ዘመን በተጀመረበት በዚህ ወቅት መሀል መርካቶ ምዕራብ ሆቴል ዙሪያ በርካታ ነጋዴዎች ችምችም ብለው የትምህርት ቁሳቁስ ሲሸጡ ተመለከትን። ሸማቹም ነጋዴዎቹ ፊት ለፊት ሆኖ ደብተር፣ እስኪሪብቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫና ሌሎች ለትምህርት አስፈላጊ ግብዓቶችን በተረጋጋ መንገድ ሲሸምት አስተውለናል። አብዛኛው ሸማች ካለፈው ዓመት አንጻር ሲታይ ገበያው እጅግ የተረጋጋና በተለይም የደብተር ዋጋ ቅናሽ የታየበት እንደሆነ ሲናገር አድምጠናል።

የትምህርት ቁሳቁስን እየሸመተች ያገኘናት ወይዘሮ ሰላም ላቀው፤ የዓለም ገና አካባቢ ነዋሪ ናት። ዘንድሮ በተለይ የደብተር ዋጋ ካለፈው ዓመት አንጻር ሲታይ ቅናሽ የታየበት መሆኑን ጠቅሳ፣ በዚህም መደሰቷን ትናገራለች። እሷ እንዳለችው፤ ባለፈው ዓመት አንድ ደብተር ከ70 እስከ 80 ብር ድረስ ተሸጧል። ሌሎች ተያያዥ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁስም እንዲሁ ዋጋቸው የሚቀመስ አልነበረም። ያም ሆኖ አንጀታችንን አስረን ልጆቻችንን ወደ ትምህርት ቤት ልከናል ስትል ያለፈውን ዓመት የትምህርት ቁሳቁስ ዋጋ ውድነት አስታውሳለች።

ዘንድሮ ደግሞ የውጭ ምንዛሪው በገበያ ዋጋ እንዲመራ መወሰኑን ተከትሎ በምግብ ሸቀጦች ላይ ጭማሪ ሲደረግ እንደነበረ ጠቅሳ፣ የትምህርት ቁሳቁስም እንዲሁ ይወደዳሉ የሚል ግምትና ፍራቻ ነበረን ትላለች። ያም ሆኖ ግን የተፈራው አልሆነም ብላለች።

የግብአቶቹ አቅርቦት ሰፊ አንደሆነ ገልጻ፣ ዋጋውም ቢሆን ካለፈው ዓመት በግማሽ ቅናሽ ታይቶበታል ስትል ጠቁማለች። በአሁኑ ወቅት በተለይም የደብተር ዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን አመልክታ፣ እንደ ጥራቱና አይነቱ ባለ50 ሉክ ደብተር ከ40 እስከ 50 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑን አስታውቃለች፤ እሷም አንድ ደብተር በ40 ብር ሂሳብ መግዛቷን ጠቅሳለች።

ገበያ ውስጥ የተለያየ ስያሜ ያላቸው አዳዲስ የደብተር አይነቶችም መግባታቸውን ተናግራ፣ ዋጋው ቅናሽ ማሳየቱም አቅርቦቱ በስፋት በመኖሩ ምክንያት ይመስለኛል።በማለት አስረድታለች፡፡

‹‹ከደብተር ውጭ ያሉ እንደ ቦርሳ፣ እስኪሪብቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ ከለር እና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁሱም ዋጋቸው እንደተፈራው አይደለም፤ ጥሩ ነው›› ያለችው ወይዘሮ ሰላም፤ አሁን ያለው ዋጋ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ነው ማለት እንጂ፤ አሁንም ቢሆን ወላጆች ልጆች ለማስተማር ብዙ ወጪ ይጠየቃሉ፤ በተለይም ጀማሪ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት የትምህርት ቁሳቁስ እየበዛ ነው። መንግሥት ይህን ቢመለከትና መስተካከል ቢችል መልካም ነው ስትል ጠቁማለች፡፡

ከልጃቸው ጋር ሆነው የትምህርት ቁሳቁስ ሲሸምቱ ያገኘናቸው ሌላኛው ወላጅ አቶ ቸርነት አያሌው እንዳሉት፤ ዘንድሮ የደብተር ዋጋ የተሻለ ነው። ሌሎች የትምህርት ቁሳቁስም ቢሆኑ ብዙም የተጋነነ ዋጋ የላቸውም። ዋናው ግን ደብተር እንደመሆኑ የደብተር አቅርቦት በስፋት አለ። ዋጋውም እንደ ጥራትና አይነቱ ከ45 ብር ጀምሮ አለ። በማለት ራዲካል አንደኛ የተባለውን ባለ 50 ሉክ ደብተር በ50 ብር ሂሳብ ለሶስት ልጆቻቸው መግዛት እንደቻሉም ተናግረዋል፡፡

ባለፈው ዓመት አንድ ደብተር እስከ 80 ብር ድረስ እንደገዙ ያስታወሱት አቶ ቸርነት ዘንድሮም ዋጋው የሚቀመስ አይሆንም ብለው እንደነበር ነው የተናገሩት። ዘንድሮ ያልተጠበቀ ለውጥ መታየቱን ጠቅሰው፣ በተለይ ደብተር ገበያ ውስጥ በስፋት በመታየቱና ዋጋውም ካለፈው ዓመት ቅናሽ በማሳየቱ መደሰታቸውን ተናግረዋል።

አጠቃላይ ገበያው የተረጋጋ ስለመሆኑ ሲገልጹ፤ ብዙ ጊዜ የተረጋጋ ገበያ የማይኖረው የአቅርቦት እጥረት ሲኖር ነው ብለዋል። ዘንድሮ ገበያው ሙሉ እንደሆነና የተለያየ አይነት ደብተር ገበያ ውስጥ እንደልብ መኖሩን ተናግረዋል። ሸማቹም አስቀድሞ መግዛቱንና አሁን ገበያው መረጋጋቱን አስታውቀዋል፡፡

‹‹የማንኛውም ዕቃ እጥረት ካለ ዋጋው ይጨምራል፤ ይህ የታወቀ ነው›› የሚሉት አቶ ቸርነት፤ የአቅርቦት እጥረት ሲኖር መንግሥት አስቀድሞ ቢሰራ መልካም ነው ይላሉ።ባለፈው ዓመት የደብተር ዋጋ አልቀመስ ብሎ ወላጆች ተማረው እንደነበር አስታውሰው፣ በወቅቱም መንግሥት ደብተር አስመጥቶ በኢትፍሩት ሱቆች በኩል ከመደበኛው ገበያ በቀነሰና ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ አቅርቦ እንደነበር ተናግረዋል።

የአዲስ ዓመት መግባትን ተከትሎ በተጀመረው የ2017 የትምህርት ዘመን የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትና ዋጋን በቃኘንበት በመርካቶ ገበያ ወላጆች የተለያዩ የትምህርት ቁሳቁስን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንደቻሉ እንዳጫወቱን ነጋዴዎችም ይህንኑ አረጋግጠውልናል። የወላጆችን ሃሳብ የተጋሩት ነጋዴዎች ዘንድሮ የትምህርት ቁሳቁስ በስፋት እንደገባ ጠቅሰው፣ ዋጋውም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ የታየበት ስለመሆኑ ተናግረዋል።

በዓለም ካለው የወረቀት ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ የደብተር ዋጋ ባለፉት ዓመታት በከፍተኛ መጠን እንደጨመረ የገለጹት አቶ ከሊፋ ዋበላ፣ የትምህርት ቁሳቁስን ሲሸጡ ነው ያገኘናቸው። አቶ ከሊፋ፣ መርካቶ ውስጥ የትምህርት ቁሳቁስ መሸጥ ከጀመሩ በርካታ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የደብተር ዋጋ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰው፣ በተለይም በ2016 የትምህርት ዘመን የደብተር ዋጋ ከፍ ብሎ ነበር ይላሉ። ይህም ለሸማቹ ተጨማሪ ጫና በመሆን ለኑሮ ወድነቱ አባባሽ ምክንያት እንደነበር ነው ያስታወሱት፡፡

አቶ ከሊፋ እንዳሉት፤ በ2017 የትምህርት ዘመን ግን የተለያዩ አይነቶች ደብተሮች ቀደም ብለው ወደ ገበያው መግባት በመቻላቸው የአቅርቦት ችግር አልገጠመም። አቅርቦቱ በቂ በመሆኑም የደብተር ዋጋ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ እየተሸጠ ይገኛል። የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ አንድ ደብተር እስከ 80 ብር ድረስ ተሸጧል፤ በአሁኑ ወቅት ግን የአንድ ደብተር ትልቁ ዋጋ 50 ብር ነው።

የደብተሩ አይነትና ጥራት የተለያየ መሆኑንም አቶ ከሊፋ ጠቅሰው፣ ዋጋውም የዚያኑ ያህል ልዩነት እንዳለው አስታውቀውዋል። ዘንድሮ አዳዲስ የደብተር ምርቶች ወደ ገበያው መግባታቸውን ተናግረው፣ ደብተሮቹ እንዲተዋወቁ በሚልም በተመጣጣኝ ዋጋ እየተሸጡ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ገበያ ውስጥ ካሉት የደብተር አይነቶች መካከል ራዲካል፣ ጋላክሲ፣ ኦርቢት፣ ሲናር ላይን ይገኙበታል። ትልቁ ዋጋ የራዲካል ሲሆን፣ ይሄውም በደርዘን ከ550 እስከ 600 ብር እየተሸጠ ነው፤ ሌሎች ጋላክሲና ሲናር ላይን እስከ 380 ብር ድረስ ይሸጣል። በማለት በ2017 የትምህርት ዘመን አጠቃላይ የትምህርት ቁሳቁስ ዋጋ ተመጣጣኝ ስለመሆኑ አብራርተዋል። በተለይም የደብተር ዋጋ ካለፈው ዓመት አንጻር ሲታይ የተሻለ መሆኑን አመልክተዋል። ዋጋው ሊቀንስ ወይም ገበያው ሊረጋጋ የቻለበት ዋናው ምክንያትም አስመጪዎች ዕቃ በብዛት ማስመጣት በመቻላቸውና የአቅርቦት እጥረት ባለመኖሩ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የተለያዩ አይነት ደብተሮችን ጨምሮ አጠቃላይ የትምህርት ቁሳቁስን እየሸጠ ያገኘነው ወጣት ሙአዝ ሙዘፋም ዘንድሮ የደብተር ዋጋ መቀነሱን አረጋግጦልናል። ለዚህም ዋናው ምክንያት የአስመጪዎች ሚና ነው ይላል።

እሱ እንደሚለው፤ ለማንኛውም ዕቃ መወደድ የአስመጪዎች ሚና ትልቅ ድርሻ አለው። የትምህርት ቁሳቁስ ደግሞ እንደሌሎች ቁሳቁስ አይደለም። የትምህርት ቁሳቁስ የሚያስመጡ አስመጪዎች ውስን ናቸው። ስለዚህ ገበያውን እንደፈለጉ ይጫወቱበታል። አስመጪዎቹ ውስን በመሆናቸው እጃቸው ላይ ያለውን የዕቃ መጠንና አይነት መሰረት በማድረግ እየተነጋገሩ ነው የሚሰሩት። ዕቃ በስፋት ሲያስገቡ ዋጋ ይቀንሳሉ፤ ዕቃውን በስፋት ካላስገቡ ዋጋ ይጨምራሉ ይህ የተለመደ አሰራራቸው ነው፡፡

የትምህርት ቁሳቁስ ላይ ሲመጣም ያው ነው። ደብተር የሚያስመጡ አስመጪዎች ጥቂት ናቸው፤ እነሱ ገበያውን እንደፈለጉ ይመራሉ። አሁን ላይ ራዲካል ደብተር አስመጪዎች በጣም ውስን ናቸው። ያም ሆኖ ግን ገበያ ውስጥ በጣም የሚፈለገውና ከፍተኛ ዋጋ የነበረው ራዲካል ደብተር ዘንድሮ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ እየተሸጠ ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት በራዲካል ስም የተለያየ ደረጃ ያለው ደብተር በስፋት ተሰርቷል። ይህም ለዋጋው መረጋጋት ትልቁ ምክንያት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በራዲካል ስም ተመሳስለው የተሰሩ ደብተሮችን ከገበያ ለማስወጣት ሲል አስመጪው ዋናውን ራዲካል ደብተር ዋጋ ቀንሶ እንዲሸጥ ማድረጉም ሌላው ምክንያት ነው ያለው ወጣት ሙአዝ፤ አንደኛው ራዲካል ደብተር አርፍዶ ወደ ገበያ መግባቱም ለዋጋው መቀነስ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ተናግሯል፡፡

በስፋት ከሚታወቀው ራዲካል ደብተር በተጨማሪ ሲናር ላይን፣ ጋላክሲ፣ ኦርቢትና ሌሎች ደብተሮችም ገበያ ውስጥ በብዛት ስለመግባታቸውና አዳዲሶቹን ለማስተዋወቅ በሚል አስመጪው ከአንደኛው ራዲካል ደብተር በተጨማሪ ነጋዴው በግዳጅ አዲስ የመጣውን ደብተር እንዲገዛ እያደረገ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

እሱ እንዳለው፤ ወደ ገበያው የገቡ አዳዲስ ደብተሮችን ለማስተዋወቅ ሲባል ሁለት ካርቶን ራዲካል ደብተር መግዛት የፈለገ ማንኛውም ነጋዴ አንድ ራዲየስ የተባለ የቻይና ደብተር እንዲገዛ ይገደዳል። አዲስና የማይታወቀው ደብተር ደግሞ ገበያው ላይ ነባር ከሆኑት ከነ ራዲካል አይነት ደብተሮች ጋር በእኩል ዋጋ መሸጥ አይችልም። ስለዚህ ከራዲካል ደብተር ጋር በተመሳሳይ ዋጋ የወጣው አዲሱ ራዲየስ ደብተር በዝቅተኛ ዋጋ እየተሸጠ ይገኛል። ምክንያቱም ሰዎች ስለማያውቁት ደፍረው አይገዙም። ከዛም አልፎ እንዲተዋወቅ በሚል በቅናሽ ዋጋ እየተሸጠ ነው፡፡

አንደኛው ራዲካል ደብተር ዘግይቶ ወደ ገበያ የገባ መሆኑን ወጣት ሙአዝ ገልጾ፤ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ዋጋው ዝቅተኛ እንደሆነ ነው ያስታወቀው። በ2016 የትምህርት ዘመን አንደኛው ራዲካል ደብተር በ900 ብር እንደተሸጠ አስታውሷል። ይሁንና በዘንድሮው የትምህርት ዘመን የደብተር ዋጋ መቀነሱ ወላጆችም ደስ እያላቸው እንዲገዙ አድርጓቸዋል። እሱ እንደሚለው የራዲካል ምርት የሆኑት ኦርቢት፣ ጋላክሲ የሚባሉ የደብተር አይነቶች ገበያ ውስጥም በስፋት የሚፈለጉ ናቸው፡፡

አጠቃላይ የደብተሮቹን ዋጋ አስመልክቶ ወጣት ሙአዝ ሲናገር፤ የዛሬ ዓመት በተመሳሳይ ወቅት 900 ብር የተሸጠው አንደኛው ራዲካል ደብተር፣ በአሁኑ ወቅት 600 ብር እየተሸጠ መሆኑን እሱም ገልጧል። የራዲካል ምርት የሆኑት ኦርቢት እና ክላሲካል 550 ብር፣ ሲናር ላይን 450 ብር እየተሸጡ መሆናቸውን አመላክቷል። ሌሎች እርሳስ፣ እስኪሪብቶ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ ከለርና የመሳሰሉት ቁሳቁስም በተመጣጣኝ ዋጋ እየተሸጡ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ በተለይም ደብተር ካለፈው የትምህርት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ዘንድሮ ሰፊ የዋጋ ልዩነት የታየበት መሆኑን አስረድቷል።



**በስፋት ከሚታወቀው ራዲካል ደብተር በተጨማሪ ሲናር ላይን፣ ጋላክሲ፣ ኦርቢትና ሌሎች ደብተሮችም ገበያ ውስጥ በብዛት ስለመግባታቸውና አዳዲሶቹን ለማስተዋወቅ በሚል አስመጪው ከአንደኛው ራዲካል ደብተር በተጨማሪ ነጋዴው በግዳጅ አዲስ የመጣውን ደብተር እንዲገዛ እያደረገ መሆኑን ጠቁሟል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ደራሲዎቻችንን ለምን ዓለም አቀፍ አላደረግናቸውም?

**ዋሰልኝ አየለ**

ሀዲስ ዓለማየሁ፣ አቤ ጉበኛ፣ ዳኛቸው ወርቁ፣ ታደሰ ሊበን.... የመሳሰሉት የኢትዮጵያ ደራሲዎች ይኖሩበት የነበረውን ዘመን ቀድመው የሄዱ፣ እንኳን የኖሩበትን ዘመን ከ100 ዓመት በኋላ የሚኖረውን ትውልድ ቀድመው የነቁ እና የሠለጠኑ ናቸው። መጽሐፎቻቸው ከተጻፉ እነሆ ከ60 ዓመታት በኋላ እንኳን እነርሱ የሳሏቸውን ገጸ ባሕሪያት ያህል አልሠለጠንም!

ሰሞኑን ፍቅር እስከ መቃብር አጀንዳ ነውና ከፍቅር እስከ መቃብር እንጀምር። በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ያለው ጉዱ ካሣ ንጥር አድርጎ የሚያሳየን የሀዲስ ዓለማየሁን አርቆ አሳቢነት ነው።በዚያ ዘመን ውስጥ ሆኖ ዛሬን የኖረ ሰው ነው፤ ዛሬ ራሱ የጉዱ ካሣን ያህል የነቃ የለም ለማለት ያስችላል። ለመብት የሚታገል፣ ኋላቀር ልማድን የሚቃወም፣ ጌታና ሎሌ የሚባል ነገር ፀረ እኩልነት መሆኑን የሚያውጅ ነበር።በዚያን ዘመን አሜሪካና አውሮፓውያን ራሱ በጉዱ ካሣ ልክ የመብትና ነፃነት ተሟጋች አልነበሩም።

አቤ ጉበኛ ‹‹አልወለድም›› ሲል ያንን አስፈሪ ንጉሣዊ ሥርዓት ይሞግታል። አቤ ጉበኛም ሆነ ሀዲስ ዓለማየሁ እንደ መንግሥት ብቻ ሳይሆን እንደ መለኮታዊ ስጦታ ይታይ የነበረውን ንጉሣዊ ሥርዓት በዚያ ልክ ይታገሉት ነበር።በዚያን ዘመን ንጉሣዊ ሥርዓቱን መድፈር መንግሥትን እንደ መተቸት ሳይሆን ፈጣሪን እንደ መዳፈር ሁሉ ይታይ ነበር። ‹‹በእንዲህ አይነት ሥርዓት ውስጥ አልወለድም›› ነው ያለው አቤ ጉበኛ። በዚያ ቀና ብሎ ማየት በማይቻልበት ዘመን ውስጥ ነው ሀዲስ ዓለማየሁ እነ አበጀ በለውን ፈጥረው ‹‹በቃ!›› ሊል የሚገባ ትውልድ መፈጠር እንዳለበት ያሳዩት።

ዳኛቸው ወርቁ ‹‹አደፍርስ›› በሚባለው ገጸ ባሕሪ (የመጽሐፉም ስም አደፍርስ ነው) ልማዳዊ የሆነውን የማኅበረሰብ አመለካከት ይሟገት ነበር።አደፍርስ የተባለበት ምክንያትም የአካባቢውን ነባር ልማድ ስለሚያደፈርስ ነው። ልክ እንደ ጉዱ ካሣ ማለት ነው።ጉዱ ካሣ ትክክለኛ ስሙ (ገጸ ባሕሪ መሆኑን ልብ እንበልና!) ካሣ ዳምጤ ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ ግን ሰውየው እብድ ስለመሰላቸው ‹‹ጉዱ ካሣ›› አሉት።አደፍርስንም ስሙን ያወጣለት የአካባቢው ሰው ነው። እነርሱ የለመዱትን ነገር ስለሚያደፈርስባቸው ማለት ነው። ዳኛቸው ወርቁ ቀድሞ የነቃ ስለሆነ እነዚያ ልማዳዊ ነገሮች እንዲቀየሩና የሰው ልጅ ነፃ ሙብት እንዲኖረው ይታገል ነበር ማለት ነው።

‹‹መስከረም›› በሚለው የታደሰ ሊበን የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ መጽሐፍ ላይ ‹‹ጅብ ነች›› የሚል አንድ አጭር ልቦለድ አለ።በነገራችን ላይ ይህ አጭር ልቦለድ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንባብ ላይ እንደነበር አስታውሳለሁ።እንደየክልሎች ሥርዓተ ትምህርት የማይኖርበትም ሊኖር ይችላል።

‹‹ጅብ ነች›› በሚለው አጭር ልቦለድ ውስጥ አሰፋ የሚባል ገጸ ባሕሪ አለ። አሰፋ ተማሪ ሲሆን አንዲት የአካባቢያቸውን ልጅ ያፈቅራል። ያፈቀራትን ልጅ ነው እናቱ ‹‹ጅብ ነች›› የሚሉት። ምክንያቱም በዘመኑ ‹‹ቡዳ›› በሚባል ልማድ ይታመን ነበር። ቡዳ የሚባሉት ደግሞ ጅብ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል። ይህ ልማድ ዛሬም የሚኖርባቸው አካባቢዎች ይኖራሉ። ታደሰ ሊበን ግን ‹‹አሰፋ›› በሚባለው ገጸ ባሕሪ ይህን ልማድ የተሟገቱት ከዛሬ 80 ምናምን ዓመታት በፊት ነው። መጽሐፉ የታተመው በ1940ዎቹ ውስጥ ሲሆን ሳይታተም የቆየበትን ደግሞ አናውቅም። ያም ሆነ ይህ ከዛሬ 70 እና 80 ዓመታት በፊት ይህን መሞገት ቀድሞ መንቃት እና መሠልጠን ነው። ምክንያቱም እነዚህ ልማዶች ‹‹የተማረ›› በሚባለው ዜጋ ሳይቀር ዛሬም አሉ።

እነዚህን አራት ደራሲዎች እንደ ማሳያ የጠቀስኩት ቀደም ያሉ ስለሆኑ እንጂ አገዛዝን የተቃወሙ ብዙ አሉ።አገዛዝን ብቻ ሳይሆን ግን ማኅበረሰባዊ ኋላቀር ልማድንም መሞገት ያስፈልጋል። ‹‹ሚንጊ ነኝ›› የሚባለውን አይነት ጎጂ ልማድ የሚሞግቱ ብዙ መጻሕፍት አሉን። እነዚህ መጻሕፍት ተደራሽነታቸው ሊሰፋ ይገባል።

ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት ከዘመን ቀድመው የነቁ ደራሲዎች እያሏት፤ ዳሩ ግን እንደነ ዶስቶየቭስኪ እና ችኑዋ አቼቤ ዓለም አቀፍ ዝነኛ አልሆኑም። ሥራዎቻቸው በብዙ ቋንቋዎች አልተተረጎሙም። ምክንያቱ ቀላል ይመስለኛል።ራሳችን እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ስላልጻፍናቸው ነው። በተለይም እንደ አሁኑ ዓለም የረቀቀ ቴክኖሎጂ ላይ ከመድረሱ በፊት መጻሕፍት ይነበቡ ስለነበር በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ተጽፈው ቢሆን ኖሮ ዓለም ያውቃቸው ነበር።በዚያው በተጻፉበት ዘመን በውጭ ቋንቋዎች ቢጻፉ ኖሮ ለዓለም የፖለቲካና የባሕል አብዮት ማሳያ ይሆኑ ነበር።ፍቅር እስከ መቃብር በእንግሊዘኛ የተተረጎመ ቢሆንም በተፈለገው ልክ አይደለም፤ አንዳንድ ቅሬታዎችም ሲነሱበት ነበር።

የችኑዋ አቼቤ ‹‹Things Fall Apart›› ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በተደጋጋሚ ስሙ ይነሳል። በተለይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ መምህራን ስለነጭ ተፅዕኖ ሲያወሩ ምሳሌ የሚያደርጉት ችኑዋ አቼቤን ነው። በአጭሩ፤ የችኑዋ አቼቤ ሙግት ነጮች በአፍሪካውያን ላይ የጫኑትን ቀንበር መሟገት ነው። ራሳቸው አፍሪካውያን ደግሞ የራሳቸውን ጥለው በውጭው ዓለም የተቃኙ፣ ከውጭውም ከራሳቸውም ሳይሆኑ የአዕምሮ መደበላለቅ የሚያጋጥማቸውና የዋዠቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

ይህ የችኑዋ አቼቤ መጽሐፍ የተወራለትን ያህል ግን የሀዲስ ዓለማየሁ ‹‹የልምዣት›› መጽሐፍ አልተወራለትም። የልምዣት የባዕድ የባሕል ወረራን ይሞግታል። አንደኛው ገጸ ባሕሪ (ባሻህ ዘለሌ ማለት ነው) የጣሊያን ወረራን የተዋጋ አርበኛ ነው። ያም ሆኖ ግን ለነፃነት ትግልም ሆነ፣ ለባሕል ወረራ ትግል በብዛት ምሳሌ የሚደረገው ከዚህ ገጸ ባሕሪ ይልቅ የውጮችን ነው።

ዋናው ነገር ለምን የእነርሱ የበለጠ ተፅዕኖ ፈጠረ የሚለው አይደለም። የእኛዎቹን እንዴት ተፅዕኖ ፈጣሪ እናድርጋቸው? የሚለው ነው።ፍቅር እስከ መቃብር በፊልም መምጣቱ እንደገና እንደ አዲስ አጀንዳ እንዲሆን አድርጎታል። መነቃቃት ፈጥሯል። ወደ ፊልም የለወጡትን ሰዎች ከልብ ልናመሰግን ይገባል፡፡

በዚያው ልክ ግን ደራሲዎቻችንን ዓለም አቀፍ የማድረግ ሥራ አልተሠራም።ባለፉት ሳምንታት ባየናቸው ሁለት ትዝብቶች እንደገለጽነው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የብዙዎች ምኞት የውጭ አገር ቋንቋ መቻልና ውጭ ሀገር መኖር ነው። በዚያው ልክ ግን የሀገራቸውን ታሪክ፣ ባሕልና ወግ በዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ቢያስተዋውቁ ጥሩ ነበር። እንዲህ አይነት መጽሐፎችን መጻፍ ባይችሉ እንኳን ቢያንስ ቢተረጉሙ ጥሩ ነበር።

ችግሩ ግን የትውልድ ክፍተት እየተፈጠረ ነው።ነባር ማንነትን ሳይለቁ ዘመኑ የደረሰበት ሥልጣኔ ላይ በመድረስ ትናንትን ማስታወስ ጥሩ ነበር።ችግሩ ግን እነ ችኑዋ አቼቤ እንዳሉት ከዚያም ከዚህም ሳንሆን የዋዠቀ ማንነት ውስጥ ገብተናል። አሁን ላይ ያሉት ዛሬን ቀድመው ነገን መጻፍ ነበረባቸው። ምክንያቱም አሁንም ኋላቀር ልማዶች አሉብን። አሁንም ፖለቲካዊ አስተዳደራችን አልሠለጠንም። አርቆ ማስተዋልን ካለፉት ደራሲዎቻችን እንማር፡፡

የኢትዮጵያ ደራሲዎች እንደ ሌሎቹ ዓለም አቀፍ ደራሲዎች ዓለም አቀፍ ዝና ያላገኙት ሀሳባቸው ከሌሎች አንሶ ሳይሆን በራሳቸው ቋንቋ ብቻ ስለተጻፈ ይመስላል።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ከቻይና እና ከሩሲያ የሚገቡ የመኪና ቴክኖሎጂዎችን ልታግድ ነው

አሜሪካ በደኅንነት ስጋት ምክንያት ለመኪና መሥሪያ የሚውሉ ከሩሲያ እና ከቻይና የሚገቡ የሶፍትዌር እንዲሁም የሃርድዌር ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገሯ በሕግ እንዳይገቡ ልታግድ ነው። አሜሪካ ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰችው ከሁለቱ ሀገራት የሚመጡ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች "ለብሔራዊ ደኅንነቴ" ያሰጉኛል በማለቷ ነው።

ባለሥልጣናት እንደሚሉት ቴክኖሎጂዎችን መከልከል ያስፈለገው በተለይም አሽከርካሪ አልባ ዘመናዊ መኪናዎችን ለማምረት የሚገቡ መሣሪያዎች ምናልባት ወደፊት በአሜሪካ ጎዳናዎች የሚሽከረከሩ መኪናዎች ከሁለቱ ሀገራት በርቀት ቁጥጥር ሊደረግባቸው እና ላልተፈለገ ዓላማ ሊውሉ ይችላሉ የሚል ስጋት በመኖሩ ነው።

ገደብ የሚጣልባቸው ቴክኖሎጂዎቹ 'ሾፌር አልባ መኪናዎችን' ለማምረት የሚያገለግሉ እና ተሽከርካሪዎች እርስ በእርስ እንዲግባቡ የሚያደርጉ የመኪና የትስስር መረብን (ኔትዎርክ) ለመፍጠር የሚያስችሉ ሶፍትዌሮች ናቸው። በአሁን ጊዜ በአሜሪካ የቻይና እና የሩሲያ ሶፍትዌር የተጫነባቸው ብዙ ተሽከርካሪዎች የሉም።

ይሁንና የአሜሪካ የንግድ ሚኒስትር ጂና ሪማንዶ "እቅዱ በተወሰኑ ሶፍትዌሮች ላይ የሚደረግ እና የአሜሪካንን ጥቅም የሚያስጠብቅ ይሆናል" ብለዋል። "መኪኖች ዛሬ ዛሬ ካሜራ፣ ማይክሮፎን፣ ጂፒኤስ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች አሏቸው። ከኢንተርኔት ጋር ተሳስረዋል። ጠላት እነዚህን መረጃዎች ካገኘ ከርቀት ላልተገባ ተግባር ሊያውላቸው እንደሚችል ለማሰብ ብዙ ጥረት አይጠይቅም። ለብሔራዊ ደኅንነታችንም የአሜሪካውያንን የግል መረጃ ለመጠበቅም ስንል እገዳውን እንጥላለን" ብለዋል።

ቻይና በበኩሏ "አሜሪካ የቻይና ድርጅቶችን ለመጉዳት ስትል ብሔራዊ ደኅንነት የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ እየለጠጠችው ነው" ስትል ወቅሳለች። የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ሊን ጂያን "አሜሪካ የንግድ ሕጎችን እንድታከብር እንሻለን። ፍትሐዊነት፣ ግልጽነት እና አንዱን ያላገለለ የንግድ ዓውድ እንዲኖር እንጠይቃለን" ብለዋል።

አሁን ውይይት ይደረግበታል የተባለው ይህ ረቂቅ በተለይ ቻይና በአሜሪካ የተሽከርካሪ ምርት ኢንዱስትሪ ውስጥ ባለው ሠንሠለት አንዳችም ቦታ እንዳይኖራት የሚያደርግ ነው። ከዚህ ቀደም አሜሪካ ከቻይና በሚገቡ የኤሌክትሪክ መኪናዎች፣ ለኤሌክትሪክ መኪና የሚሆኑ ባትሪዎች እና በሌሎችም ከቻይና በሚገቡ ቁሳቁሶች የታሪፍ ጭማሪ ማድረጓ አይዘነጋም።

አሁን በሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ምርት ላይ የሚጣለው ገደብ ከፈረንጆቹ 2027 በኋላ በሚመረቱ የመኪና ሞዴሎች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ነው። በሃርድዌር ላይ የሚጣለው ገደብ ደግሞ ሕጉ ከወጣ ከሦስት ዓመት በኋላ ተግባራዊ የሚሆን ነው። ይህም በአሜሪካ የተሽከርካሪ ኢንዱስትሪው ሌላ አማራጭ እንዲያገኝ ጊዜ ለመስጠት የታሰበ ነው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## ጃፓን ጎብኚዎችን ለማበረታታት የአውሮፕላን ቲኬት በነፃ አቀረበች

ጃፓን ጎብኚዎችን ለማበረታታት የአውሮፕላን ቲኬት በነፃ አቀረበች፡፡ የሩቅ ምሥራቋ ጃፓን ሀገሯን ለሚጎበኙ ጎብኚዎች ነፃ የጉዞ ቲኬት እንደምትሰጥ ገልጻለች፡፡ የሀገሪቱ ቱሪዝም ቢሮ እንደገለጸው ጃፓንን ለሚጎበኙ ጎብኚዎች የሀገር ውስጥ በረራ ለማድረግ ነፃ የጉዞ ቲኬት ማዘጋጀቱን አስታውቋል፡፡

የነፃ ጉዞ ፕሮግራሙ የተዘጋጀው በጃፓን አየር መንገድ በኩል ለሚጓዙ መንገደኞች ሲሆን ዋና ዓላማውም የጎብኚዎችን ቁጥር ለመሳብ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተለይም በገጠራማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚጓዙ ጎብኚዎች የበለጠ እና የተሻለ የጉዞ ማበረታቻዎች ተሰጥተዋል፡፡ የአሁኑ የነፃ ጉዞ ቲኬት ዋጋ በጎብኚዎች ለሚጨናነቁ ቦታዎች እፎይታ ለመስጠት፣ ገጠራማውን የሀገሪቱ ቦታዎችን ለማስጎብኘት እና ከቱሪዝም የተሻለ ገቢ ለማግኘት ያለመ እንደሆነም ተገልጿል፡፡

ዩሮ ኒውስ እንደዘገበው ከሆነ ጎብኚዎች ይህንን ዕድል ለማግኘት መጀመሪያ በጃፓን አየር መንገድ መጓዝ እና የሀገር ውስጥ በረራዎች ቲኬት መግዛት ይጠበቅባቸዋል፡፡ አየር መንገዱ 24 ሰዓት እና ከዛ በላይ በጃፓን ለሚቆዩ መንገደኞች ለሀገር ውስጥ በረራ ያወጡትን ገንዘብ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

እንዲሁም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን የአሜሪካ፣ ካናዳ፣ ሜክሲኮ፣ ታይላንድ፣ ሲንጋፖር፣ አውስትራሊያ፣ ቻይና ሕንድ፣ ፊሊፒንስ እና ሌሎችም ሀገራት ዜግነት ሊኖራቸው ይገባል ተብሏል፡፡ በቀጣይም ጃፓን ለተጨማሪ ሀገራት ጎብኚዎች ይህን የነፃ ጉዞ ቲኬት ዕድል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ማስታወቁን አል ዐይን ዘግቧል፡፡



# በቀጣናው የግብጽን የጥፋት ተልእኮ ለመመከት

**ኤልያስ ጌትነት**

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስትራቴጂክ ከሚባሉ አካባቢዎች አንዱ እና ዋነኛው ነው።አካባቢው ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሊያን የሚገኙበት ትልቁ የዓለማችን የባሕር ላይ ንግድ መስመር ነው። በቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ የሚገኘው የባብል ኤል-ማንደብ ሰርጥ የዓለማችን 15 በመቶ የሚሆን የንግድ መርከቦች እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ስፍራ መገኛ ነው። አካባቢው ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከአፍሪካ እና ከእስያ ሀገራት የተለያዩ ምርቶች ወደ አውሮፓ እና አሜሪካ የሚተላለፉበት ወሳኝ መስመር ነው።

አካባቢው ካለው ከዚህ ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አኳያም ከቀደሙት ዘመናት አንስቶ አካባቢው የብዙዎችን ቀልብ እየሳበ የሚገኝ ነው። ያደጉት ሀገራትም በአካባቢው ያላቸውን ብሔራዊ ጥቅሞች ተጨባጭ ለማድረግ በአካባቢው ከሚገኙ ሀገራት ጋር ወዳጅነትን በመመሥረት ተጽዕኗቸውን እና ቁጥጥራቸውን ለማጠናከር የሚሽቀዳደሙበት ነው።

አሜሪካ፣ ፈረንሳይ ሩስያ፣ ቻይና እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ በቀጠናው /በጅቡቲ የጦር ሠፈሮችን አቋቁመው ወታደሮቻቸውን በማስፈር አለኝ የሚሉትን ጥቅሞቻችውን ለማስጠበቅ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል። ለምሳሌ ያህል አገራቱ የጦር ሠፈሮች፣ የባሕር ኃይል ወደቦች፣ አየር ኃይል እና ማሰልጠኛ ማዕከላትን ጭምር በጂቡቲ ገንብተዋል።

የአካባባው ሀገራት ሕዝቦች ግን ከቅኝ ግዛት ውርስ እና ከራሳችው ውስጣዊ ችግሮች በሚመነጩ የተለያዩ ምክንያቶች በሚቀሰቀሱ ጦርነቶች እና በድርቅ የእለት ተእለት ሕወታቸው ሲፈተን እና አለመረጋጋት እና የሰላም እጦት ሲዳረጉ ማየት የተለመደ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

በተለያየ ወቅቶች በነዚህ ችግሮች የተፈተነችው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀደሙት ጊዜያት ከነበራት አንጻራዊ ሰላም እና ጠንካራ የመከላከያ ኃይል አኳያ፤ አስቸጋሪ በሚባሉ ወቅቶች ሳይቀር ለቀጣናው ሰላም እና መረጋጋት ግንባር ቀደም በመሆን ዓለም አቀፍ እውቅና ባገኘ መልኩ ስትንቀሳቀስ ቆይታለች፤ በዚህም ያበረከተችው እና እያበረከተች ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

የቀጠናውን ሰላም እና መረጋጋት በራሷ ሰላም እና ደህንነት ላይ የሚኖረው አዎንታዊ አስተዋጽዖ ግምት ውስጥ በማስገባት በጎረቤት ሀገራት የሰላም አስከባሪ ወታደሮቿን ልካ ብዙ መስዋዕትነት ከፍላለች፤ ዛሬም እየከፈለች ነው። ይህ በሀገራቱ ሕዝቦች የወንድማማችነት ታሪክ ውስጥ የጎላ ስፍራ እንደሚኖረው ይታመናል።

በተለይም በሶማሊያ የተሰማራው የኢትዮጵያ የሰላም አስከባሪ ኃይል የሶማሊያን ሕዝብ እና መንግስት ከአልሸባብ እና ሌሎች ፅንፈኛ ኃይሎች በመታደግ ሂደት ወስጥ የነበረው የጎላ አስተዋጥኦ፤ በተለይም የችግሩ ዋንኛ ገፈት ቀማሽ በነበረው የሶማሊያ ሕዝብ ሕሊና ውስጥ በቀላሉ ሊፋቅ የሚችል አይደለም።

ይህ በብዙ የመስዋእትነት ደም የተጻፈ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የክፉ ቀን አጋርነት፤ አሁን አሁን በሶማሊያ መንግስት በኩል ተገቢውን ከበሬታ እያጣ፤ የሀገሪቱን ሕዝብ ዳግም ለከፋ አደጋ፤ ሀገሪቱንም ለተጨማሪ የመከፋፈል ስጋት የሚያጋልጡ እውነታዎች መታየት እና መሰማት ጀምረዋል።

በተለይም በኢትዮጵያ እና ሶማሌ ላንድ መካከል በወደብ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የመግባቢያ ስምምነት መፈረሙን ተከትሎ፤ በሞቃዲሾ መንግስት በኩል ከተሳሳተ ግንዛቤ በመነሳት እየተወሰዱ ያሉ የጠብ አጫሪነት እርምጃዎች ቀጣናውን ወደ አላስፈላጊ ቀውስ ሊወስዱ እንደሚችሉ እየተገመተ ነው ፡፡

**እስከ አምስት ሺህ የሚደርሱ የግብፅ ወታደሮች በዓመቱ መጨረሻ አዲስ በሚደራጀው የአፍሪካ ሕብረት የሰላም አስከባሪ ኃይል ውስጥ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ያላት ፍላጎትም ለሱማሊያ አለመረጋጋት እና ለአፍሪካ ቀንድ ቀጣናዊ ተጨማሪ የግጭት ምንጭ ሊሆን እንደሚሆን በብዙዎች ዘንድ ስጋት የፈጠረ ነው**

የሶማሊያ መንግስት እየወሰዳቸው ያሉ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ጋር የሚጋጩ እርምጃዎችን፤ በተለይም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት ከሆነችው ግብጽ ጋር እየፈጸመ ያለው ያልተቀደሰ ጋብቻ፤ ለአካባቢው ሰላም እና መረጋጋት ተጨማሪ ስጋት እየሆነ ነው። በተለይም የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩን በጥንቃቄ እንዲመለከተው እያስገደደው የሚገኝ ክስተት ሆኗል፡፡

ግብጽ በዋነኝነት በቀይ ባሕር እና የስዊዝ ቦይ (Suez Canal) ላይ ባላት ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ምክንያት የቀይ ባሕር የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በተጽዕኖዋ ስር እንዲሆን ትፈልጋለች። እነዚህ ፍላጎቶቿ የቀይ ባሕር የንግድ መስመሮችን መቆጣጠር፣ የባሕር በር ይዞታዋን ማስፋት፣ ጠንካራ የባሕር ኃይል እንዲኖራት መፈለግ ብሎም የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካን በራሷ ፍቃድ በሚዘወሩ መንግስታት እንዲከወን ማድረግ ዘመናት የተሻገረ ምኞቷ ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ የአባይ ውሃ ምንጭ በሆነቸው ሀገራችን ሰላም እንዳይሰፈን ለማድረግ ከቅኝ ግዛት በተሻገረ ሕልሟ የአባይን ውሃ በብቸኝነት ለመጠቀም ትፈልጋለች። ይህንን ፍላጎቷ ለመፈፀም አሁን ላይ ኢትዮጵያ እና ሱማሌላንድ ያደረጉትን ስምምነት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ራሷን የሶማሊያ አጋር አስመስላ እየተንቀሳቀሰች ነው። ወደ ሶማሊያ እጇን ለማስገባት እየሞከረች ያለውም የቀጣናውን ሰላም ለማደፍረስ ብሎም ለኢትዮጵያ እድገት እንቅፋት ለመሆን ነው ፡፡

በሶማሊያ እና በግብፅ መካከል የተካሄዱ የትብብር ስምምነቶች፤ ወታደራዊ ስምምነትን ጨምሮ የዚሁ እውነታ አካል ነው። ወትሮም ቢሆን ሰላም በራቀው የአፍሪካ ቀንድ ላይ ከቀጣናው ፍላጎት ውጭ የሆነ ኃይል እጁን ሲያስገባ ይዞት ሊመጣ የሚችለው ቀውስ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ስምምነቱን ተከትሎ ኢትዮጵያ ጉዳዩ በብሔራዊ ጥቅሟ እና ሉአላዊነቷ ላይ ይዞ ሊመጣ የሚችለው ጫና በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ በጥንቃቄ እየተከታተለች ትገኛለች።

እስከ አምስት ሺህ የሚደርሱ የግብፅ ወታደሮች በዓመቱ መጨረሻ አዲስ በሚደራጀው የአፍሪካ ሕብረት የሰላም አስከባሪ ኃይል ውስጥ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ያላት ፍላጎትም ለሱማሊያ አለመረጋጋት እና ለአፍሪካ ቀንድ ቀጣናዊ ተጨማሪ የግጭት ምንጭ ሊሆን እንደሚሆን በብዙዎች ዘንድ ስጋት የፈጠረ ነው፡፡

ለሶማሊያ ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለውን አልሸባብ በመዋጋት ረገድ ቁልፍ አጋር ከሆነችው ኢትዮጵያ ይልቅ በችግሯ ጊዜ ምንም አስተዋጽዖ ካላደረገችው ግብጽ ጋር የጫጉላ ሽርሽር በሚመስል ሁኔታ ላይ መገኘቷዋ ግብጽ አካባቢውንም ለማመስ ላላት ፍላጎት ፈረስ ሁነው ለማገልገል ያላቸውን ዝግጁነት ያሳየ ነው፡፡

ግብጽ ከዚህ ቀደም ኢትዮጲያ በራሷ አቅም የምትገነባው የአባይ ግድብ ለማስቆም ተደጋጋዊ ጥረቶችን ስታደርግ ቆይታለች ፤ጥረቶቿ በኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት ጥንካሬ ከንቱ ሆኖ ግንባታው ፍጻሜ ላይ ደርሷል ፤ይህ ዛሬም ድረስ አልዋጥላት ያላት ግብጽ በሶማሊያ በኩል አካባቢውን ወደ ግጭት በመግፋት የአካባቢውን ሀገራት ህዝቦች የመልማት ፈግላጎት ፈተና መሆን ትፈልጋለች።

ይህን የግብጽ ወቅታዊ ስጋትነት ተቋቁሞ ለመሻገር ኢትዮጵያውያን እንደቀደሙት ዘመናት አንድነታቸውን አጠናክረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ለሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም በጋራ መቆም ፤የውስጣዊ ችግሮቻችን በውይይት መፍታት ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል ። ለዚህም ግብጽ በአፍሪካ ቀንድ ልትወስዳቸው የምትችላቸው ቀጣይ ተግባራት ምን ሊሆኑ ይችላሉ የሚሉ አንዳንድ ነጥቦችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ አመክራለሁ።

ግብፅ አሁን እንደሚስተዋለው የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስትን ለጥፋት ፍላጎቷ ማስፈጸሚያ አድርጋ መጠቀሟ የማይቀር ነው ።በርግጥ ግብጽ እራሷ በቀሰቀሰቻቸው ጦርነቶች በታሪኳ በአንዱም ኢትዮጵያን አሸንፋ አታውቅም ። ከዚህ ታሪካ እውነታ እና አሁን ላይ ኢትዮጵያ ያለችበትን አቅም በማጤን ከኢትዮጵያ ጋር የቀጥታ ጦርነት ውስጥ ትገባለች ተብሎ አይታሰብም ፡፡

ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር ወደ ቀጥተኛ ጦርነት ልትገባ የማትፈልገው ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ብሔራዊ አንድነት እና ነጻነት ምን ያህል ዋጋ እንደሚከፍሉ ስለምታውቅ ብሎም ተሳስታ የጦርነት ካርድን ብትመዝ ሊያስከትልባት የሚችለውን ከባድ አጸፋ ስለምታውቅ ነው።

ይህም እንዳለ ሆኖ በሶማሊያ ያለው መንግስት ደካማ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ጸረ ኢትዮጵያ ኣቋም ያለው እንዲሆን እና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚጻረሩ የተለያዩ እርምጃዎችን እንዲወስድ በማድረግ የቀጣናውን ሰላም ለመበጥበጥ የጀመረችውን ጥረት አጠናክራ ልትቀጥልበት ትችላለች። ኢትዮጵያ በበሶማሊያ ያለው የማዕከላዊ መንግስት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የማይጻረር እና ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር መስራት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ቀዳሚ እርምጃዋ መሆን አለበት፡ ፡

ሌላኛው ጉዳይ ግብጽ የተለያዩ ጽንፈኛ አካላትን ልታስታጥቅ የምትችልበት እድል መኖሩ ነው። ይሄም በሶማሊያ አልሸባብን ጨምሮ የተለያዩ አሸባሪ ኃይሎችን በመደገፍ ቀጣናው የሽብርተኞች እና ወንበዴዎች መናሃሪያ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ አካሄድ ሊኖራት ይችላል። ይሄም ግብጽ በኢትዮጵያ የሽብር ጥቃቶችን እንዲፈጽሙ በማድረግ የኢትዮጵያን ሰላም አደጋ ውስጥ ለመከተት ልትሞክር ትችላለች ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ግብጽ ልትከተለው የምትችለው ሌላው የጥፋት አማራጭ በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ጫና ለመፍጠር የሚደረግ ሙከራዎችን ማድረግ ነው። ግብጽ በውክልና ጦርነት የኢትዮጵያን ሰላም ለመበጥበጥ ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪ ሌላኛው ጉዳይ የኢኮኖሚ ጫና ለመፍጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለመውሰድ የምታደርገው ጥረት ሊኖር ይችላል፡፡

በተለይም ከሶማሊያ በዘለለ ግብጽ ወደ ጅቡቲ በመጠጋት የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮችን ልትፈጽም የምትችልበት እድል እንዳይኖር ከጅቡቲ ጋር ያለን ግንኙነት አሁን ካለበት በላይ ማጠናከር የሚያስችል ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የግብጽን እኩይ ሴራዎች ለመከላከል ቀጣናዊ ጥምረቶችን በማጠናከር ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት የምትከተለውን መንገድ አጠናክራ መቀጠል፤ በምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስት (ኢጋድ) በኩል ቀጠናዊ ችግሮች ለመፍታት የምታደርጋቸውን ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርባታል።

በኢጋድ ውስጥ ያላትን አዎንታዊ አስተዋጽዖ በማሳደግ ከሀገሪቱ የሰላም እና ደህንነት ሁኔታ በዘለለ ለምስራቅ አፍሪካ ቀጣናዊ ሰላም እና የኢኮኖሚ ትብብር እንዲጎለብት ማድረግ፤ (ኢጋድ) በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል የተፈጠረውን ፖለቲካዊ ውጥረት በድርድር ለመፍታት የጀመረውን ጥረት በማገዝ ፖለቲካዊ ትኩሳቱ እንዲቀዛቀዝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ አጋር አካላት ጋር በተለይም እንደ አሜሪካ፣ የአውሮፓ ሕብረት እና የአፍሪካ ሕብረት የመሳሰሉ ተቋማት አዎንታዊ ድጋፍ እንድታገኝ ያላሰለሰ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት በማድረግ የግብጽን ጸብ አጫሪ ድርጊቶች ማምከን ያስፈልጋል።

አዋሽ ኢንሹራንስ Awash INSURANCE We Flow with You

# የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 366(1)፣367(1)፤370፣393(1) እና 400(1) እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 8(ሀ) መሠረት የአዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔና 12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ቅዳሜ ጥቅምት 16 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

## 1. አክሲዮን ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ:- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 7 አዋሽ ታወርስ ላይ ይገኛል።

Website: www.awashinsurance.com

1.2. የንግድ ምዝገባ ቁጥር፡- አአ/ንግ-3-1532/87

1.3. የመድን ሥራ ፍቃድ ቁጥር- 003/94

1.4. እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2024 ላይ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) -ብር 3,850,185,500

1.5. እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2024 ላይ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)- ብር 1,921,492,300

## 2. የ30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1. እ.ኤ.አ. በ2023/24 የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮች፣ የአዲስ አክሲዮኖች ሽያጭና አዲስ ባለአክሲዮኖችን ማሳወቅ፣

2.2. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.3. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.4. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የትርፍ ክፍፍል ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ማፅደቅ፤

2.5. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፣

2.6. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የዲሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል መወሰን፤

2.7. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የኦዲተሮችን ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፤

2.8. የዲሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ማካሄድ።

## 3. የ12ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ

-የአዋሽ ኢንሹራንስ ኢማ መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል፡፡

## 4. ማሳሳቢያ

4.1. በጉባዔዎቹ ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋና መሥሪያ ቤቱ 2ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው በማህበሩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ አላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው።

4.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**የአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. ዲሬክተሮች ቦርድ**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## አዳዲስ ከዋክብት ለፈጣን ሰዓት የሚፋለሙበት የበርሊን ማራቶን

**ቦጋለ አበበ**


ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ወር መስከረም ከሚያደርጓቸው ውድድሮች መካከል የበርሊን ማራቶን ተጠባቂው ነው። በርካታ የዓለም የማራቶን ኮከቦች በሚፋለሙበት በዚህ ውድድር ከሁለት ሳምንት በኋላ ሲካሄድ ኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ የሚያደርጉት ፉክክር እንደወትሮው በጉጉት ይጠበቃል።

በተደጋጋሚ የርቀቱ የዓለም ክብረወሰን በሚሰበርበት የበርሊን ማራቶን ከ2014 በኋላ የርቀቱ ፈርጦች ቀነኒሳ በቀለና ኢሉድ ኪፕቾጌ በዘንድሮው ውድድር አይሳተፉም። ይህም የአሸናፊነቱ ቅድመ ግምትና የዓለም ክብረወሰን የማሻሻል ተስፋው በአዳዲስ የርቀቱ ከዋክብት ትከሻ ላይ ወድቋል።

በወንዶች መካከል በሚደረገው ፉክክር 42 ኪሎ ሜትሩን ከ2:05 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ስድስት አትሌቶች ይሳተፋሉ። በሴቶች መካከል ደግሞ ከ2:20 በታች ያጠናቀቁ አራት አትሌቶች እንዲሁም ከ2:22 በታች የፈፀሙ አስር አትሌቶች ተሳታፊ ናቸው። ከነዚህ መካከል ከ2፡16 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ሁለት አትሌቶች ይገኙበታል።ባለፈው ዱባይ ማራቶን በርቀቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈች አትሌት በተመዘገበ ፈጣን ሰዓት 2:16:07 ያሸነፈችው ትዕግስት ከተማ አንዷ ስትሆን በቶኪዮ ማራቶን ሁለተኛ ሆና ያጠናቀቀችው ኬንያዊቷ ሮስማሪ ዋንጂሩ ሌላኛዋ አትሌት ነች።

በርሊን ላይ የመጀመሪያ ውድድሯን የምታደርገው ትዕግስት ባለፈው ዓመት በዚሁ ውድድር የዓለም ክብረወሰን የሰበረችውና የኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀችው ኢትዮጵያዊት አትሌት ትዕግስት አሰፋ የልምምድ አጋር ስትሆን ወደ በርሊን የምታቀናው ቀዳሚውን ፈጣን ሰዓት ይዛ ነው።




**አትሌት ታደሰ ታከለና ትዕግስት ከተማ በዘንድሮው በርሊን ማራቶን ስድል ይጠበቃሉ፣**

ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት ይዛ በውድድሩ የምትሳተፈው ዋንጂሩ ከሁለት ዓመት በፊት የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን በርሊን ላይ አድርጋ ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ 2:18:00 በማስመዝገብ ነበር። ይህን ሰዓት ባለፈው ቶኪዮ ማራቶን ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ ወደ 2:16:14 አሻሽላለች። ይህ ያሳየችው እድገትም ዘንድሮ ቶኪዮ ላይ ትኩረት እንዲሰጣት አድርጓል።

የቀድሞዋ የ1500 ሜትር ባለክብረወሰን ገንዘቤ ዲባባ ከመካከለኛ ርቀት ወደ ማራቶን ፊቷን ካዞረች ወዲህ አጀማመሯ ጥሩ ቢሆንም ብዙ ርቀት አልተጓዘችም። ዘንድሮ ግን በርሊን ላይ የማራቶን ታሪክን በፈጣን ሰዓት ለማድመቅ ትሮጣለች። ገንዘቤ ከሁለት ዓመት በፊት የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን አምስተርዳም ላይ አድርጋ 2:18:05 ማጠናቀቅ እንደቻለች ይታወሳል። ይህንን ሰዓትን ግን ባለፉት ሁለት ዓመታት ማሻሻል አልቻለችም። ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት የብርጓል መለሰ በ2:19:36 ርቀቱን ከ2፡20 በታች ማጠናቀቅ ከቻሉ አራት አትሌቶች አንዷ ስትሆን ዘንድሮ በርሊን ላይ ጠንካራ ተፎካካሪ ከሚሆኑ ኮከቦች መካከል ስሟ ይገኛል። መስታወት ፍቅር (2:20:45)፣ አዝመራ ገብሩ (2:20:48)፣ ሲሳይ ጎላ (2:20:50)፣ አባብል የሻነህ (2፡20፡51)በውድድሩ የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

በወንዶች መካከል በሚደረገው ፉክክርም ቀዳሚውን ፈጣን ሰዓት የያዘው ኢትዮጵያዊው አትሌት ታደሰ ታከለ ነው።2:03:24 ምርጥ ሰዓቱ ሲሆን ሁለተኛና ሦስተኛውን ፈጣን ሰዓት ይዘው ከሚወዳደሩት ኬንያውያን አትሌቶች ሮናልድ ኮሪር (2:04:22)፣ ሳይብሪያን ኮኩት (2:04:34) ጋር የሚያደርገው ፉክክር ተጠባቂ ነው። ታደሰና ኮሪር ባለፈው በርሊን ማራቶን ሦስተኛና አራተኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁ አትሌቶች መሆናቸው ይታወሳል። ኃይለማርያም ኪሮስ (2:04:41)፣ ባዘዘው አስማረ (2:04:57)፣ሚልኬሳ መንገሻ(2:05:29)፣ ሃይማኖት አለው (2:05:30) በውድድሩ የሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

እኤአ ከ1974 ጀምሮ እየተካሄደ የሚገኘው የበርሊን ማራቶን ከዓለም አምስቱ ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች አንዱ ሲሆን፣ ዘንድሮ ሃምሳኛ ዓመቱን ያከብራል። በውድድሩ የግማሽ ክፍለ ዘመን ጉዞ አስራ ሦስት ያህል የዓለም የማራቶን ክብረወሰኖች የተሰበሩበት ሲሆን ይህም ከሌሎች የማራቶን ውድድሮች የተለየና አትሌቶች ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ እንዲመርጡት አድርጎታል። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሃምሳኛ ዓመቱን ሲያከብርም ከአትሌቶች በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሃምሳ ሺ በላይ ሕዝብ እንደሚሳተፍ ይጠበቃል፡፡

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY
ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የምግብ ዘይትና ዱቄትን በማበልፀግ አስገዳጅ ደረጃን እውን የማድረግ ጅማሮ

የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ጥናት እንደሚያመላክተው፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ ከተመጣጠነ ምግብ እጥረት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ተግዳሮቶች እየገጠሟት ይገኛል፡፡ መረጃው በአሁን ወቅት በሀገሪቷ የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ቪታሚኖችና ማዕድናት እጥረት ከፍተኛ ሁኔታ ስለመኖሩና በተለይም የቫይታሚን ኤ፣ዲ፣ቢ ኮምፕሌክስና ዚንክ ንጥረ ነገሮች እጥረት ጎልቶ እንደሚታይም ይጠቁማል፡፡ የእነዚህ ንጥረ ነገሮች እጥረት በተለይም በፅንስ ውስጥ ባሉና በማደግ ላይ ባሉ ሕጻናት እንዲሁም ሴቶች ላይ ተንሰራፍቶ ይገኛል።

የቫይታሚን ቢ ኮምፕሌክስ እጥረት ድካም፣ የግንዛቤ ችግሮችና የደም ማነስን ሲያስከትል፣ የዚንክ እጥረት ደግሞ የሰውነትን በሽታ የመከላከል ሥርዓትን ስለሚጎዳ ግለሰቦች ለኢንፌክሽን በቀላሉ እንዲጋለጡ ምክንያት ይሆናል፡፡

ቫይታሚን ኤ ከዓይን ጋር ያለ ችግር እንዲሁም ከፎሌት ወይም ከብረት ማዕድን ጋር በተያያዘ ደግሞ ኤን ቲ ዲ (Neural tube defects) ሕፃናት ገና ሲወለዱ ጀርባቸው ላይ እብጥ ብሎ የሚታይ ጭንቅላታቸው በጣም ትልቅ ሆኖ ውሃ የሚቋጥር እንዲሁም ቁመትና ክብደት ያለመመጣጠን ማለትም ቅንጨራ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ሊከሰቱ የቻሉት አስፈላጊ የሆኑ ቫይታሚኖችና ማዕድናት በበቂ መጠን በምግብ ውስጥ አለማግኘት ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር ዋና ዋና ምግቦችን ለማበልፀግ አስገዳጅ ደረጃዎችን አውጥቷል። ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ባልተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምክንያት የሚመጣውን በሽታና ሞት ለመቀነስ እንዲሁም በተለይ በሕጻናት፣ እርጉዝ ሴቶችና አረጋውያን ባሉ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል የምግብ ንጥረ ነገሮችን እጥረት ለመከላከል ያለመ ነው፡፡

ይህ ምግቦችን በንጥረነገሮች ማበልፀግ አዲስ ጽንሰ-ሐሳብ ሳይሆን በበርካታ ሀገራት በአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚመገበውን የምግብ አይነት እየመረጡ የሚተገብሩት ነው፡፡ እንደ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ካናዳና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ሀገሮች ዱቄትንና ሌሎች ምግቦችን ማበልፀጋቸውን የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ሀገራችንም መሰል እርምጃዎችን በሂደት ላይ ትገኛለች፡፡ የምግብ ዘይትና ዱቄት እንዲበለፅጉ አስገዳጅ ደረጃዎች ሲወጣላቸው ዱቄት (አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ) CES 390 በቫይታሚን ቢ ምድቦች በሆኑት በቢ ኮምፕሌክስና በዚንክ እንዲሁም የምግብ ዘይት (አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ) CES 310 በቫይታሚን ዲ እና ኤ እንዲበለፅግ የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎችም ከውጭ ማስገባት ያለባቸውን ማበልፀጊያውን (fortificant) እና የማበልፀጊያውን ማሽን እንዲያሟሉ በማድረግ ይሄንን የማበልፀግ ሥራ እንዲሠሩ ከአንድ ዓመት በላይ የእፎይታ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን አሁን የእፎይታ ጊዜው ተጠናቆ ወደትግበራ እንዲገቡ ይጠበቃል። ይህንኑ ተከትሎ የቁጥጥር ሥራውም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

እንዲበለፅጉ የተመረጡት የምግብ አይነቶች የተመረጡበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ አብዛኛው ኅብረተሰብ በየቀኑ የሚጠቀማቸው እንዲሁም ለማበልፀግ ቀላል የሆኑ በመሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለመግዛትም ተመጣጣኝ የሆኑና በቀላሉ ማግኘት የሚቻሉ የምግብ አይነቶች በመሆናቸው ጭምር ነው፡፡

ለምሳሌ ዱቄት ሲመረጥ በብስኩትም፣ በዳቦም በሌላም መልኩ፣ ዘይት ሲባል እያንዳንዱ የሚዘጋጀው ምግብ ውስጥ አብዛኛው ሰው ዘይት ይጨመራል፤ ጨውም በተመሳሳይ ሁኔታ አብዛኛው ጊዜ ምግብ ለማጣፈጥ የምንጠቀምበት ግብዓት ስለሆነ ነው፡፡

በጨው ላይ ያለው አስገዳጅ ቀድሞ እየተተገበረ ያለ ሲሆን በዱቄትና ዘይት ላይ አስገዳጅ ደረጃውን ከሐምሌ አንድ ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በዚህም መሠረት ተቆጣጣሪዎች በአሁን ጊዜ ገበያ ላይ ያለው የምግብ ዘይትና ዱቄት በደረጃው መሠረት የበለፀገ መሆኑን የመቆጣጠር ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣንም አስገዳጅ ደረጃውን ለማስፈፀም በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት በባለፈው ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በቅርንጫፍና በመውጫና መግቢያ እንዲሁም ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት የተግባርና የንድፈ ሃሳብ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለተቆጣጣሪ ባለሙያዎች በዩኒሴፍ የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት በመስጠት ወደትግበራ ገብቷል።

በአቅም ግንባታ ሥልጠናው በተለይ ዘይት ውስጥ ያለውን የቫይታሚን ኤ መጠን ለማረጋገጥ የሚያስችል ፈጣን የሆነ አስራ ሁለት የመመርመሪያ ኪቶች በተለያየ ጊዜ ከዩኒሴፍ በድጋፍ ተሰጥተው ለቅርንጫፎችና ለመግቢያና መውጫ ኬላዎች እንዲያገኙና ለሁለት ክልሎችም ድጋፍ እንዲያገኙ የተደረገበት ሁኔታ ቢኖሩም በቀጣይ ሁሉም ክልሎችና፣ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ቢሮዎች እንዲሁም ዋናው መሥሪያ ቤት በበቂ መጠን የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ ታምኖበታል።

በዘርፉ የአቅም ግንባታ ለማድረግ ለሠልጣኞች በተሰጠው ሥልጠና ለሠልጣኞች ከንድፈ ሀሳብ ባሻገር እነዚህ ፈጣን የመመርመሪያ ኪቶች እንዴት መመርመር ይችላሉ የሚለውን ለመገምገም በቫይታሚን ኤ እና ዲ የበለፀገ ዘይት ከገበያ ተገዝቶ ሙከራ ተደርጎ በተግባር ዕውቀት አግኝተው እንዲሄዱ ተደርጓል፡፡ እነዚህን አስገዳጅ ደረጃዎች ተፈፃሚነታቸውን ለመከታተል ደግሞ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱና የክልል ጤና ግብዓቶች ተቆጣጣሪ አካላት ሚናቸው ላቅ ያለ ነው፡፡

እነዚህን አስገዳጅ ደረጃዎች ገቢራዊነታቸውን ለመከታተልም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ መንገዶችን የሚጠቀም ሲሆን በምግብ አምራች ፋብሪካዎች፣ በገበያዎች፣ በመግቢያና መውጫ ኬላዎች የኢንስፔክሽን ሥራዎችን መሥራት አንዱ ሲሆን እንዲሁም ዶክመንቶችን በመፈተሽ ምግቦችን መመዝገብና በላቦራቶሪ በኩል ደግሞ የጥራት ቁጥጥር የማድረግ ሥራዎችን በስፋት ይሠራል፡፡

ዱቄትን በቫይታሚን ቢ ኮምፕሌክስና ዚንክ እንዲሁም የምግብ ዘይቶችን በቫይታሚን ኤ እና ዲ የግዴታ ማበልፀጉ ሀገራችን የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመከላከል በምታደርገው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ አበርክቶ አለው። እነዚህን አስገዳጅ ደረጃዎች ተግባራዊ በማድረግ ሀገሪቱ አፋጣኝ የሆኑትን የኅብረተሰብ ጤና ስጋቶች ከመፍታት ባለፈ ጤናው የተጠበቀና አምራች ዜጋን የመገንባት ውጥኗን ለማሳካት ያስችላታል።

ልጆች የአዕምሮ ብስለታቸው እድገት እንዲጨምርና የበሽታ መከላከያ አቅማቸው እንዲጎለብት፣ ሴቶች ጤናማ እርግዝና እንዲኖራቸው እና አዋቂዎች አጠቃላይ ጤናቸው ተጠብቆ ምርታማ እንዲሆኑ በማድረግ ሀገሪቷ የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን በመቀነስ የሕዝቦቿን ደኅንነት ለማሻሻል ይህ ምግብን የማበልፀግ ተግባር ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል።

በመጨረሻም የኅብረተሰብ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት በየጊዜው ጥናቶችን የሚያከናውን በመሆኑ የዚህ አስገዳጅ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ መሆን በኅብረተሰቡ ጤና ላይ የፈጠረውን ለውጥ በጥናቱ ውጤት መሠረት ወደፊት የሚታይ ይሆናል፡፡

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/